# በኢየሱስ እናምናለን

## ትምህርት አንድ

## ነጻ አውጪው/ ቤዛችን

# We Believe in Jesus

## Lesson One

## The Redeemer

THIRD MILLENNIUM
MINISTRIES
Biblical Education. For the World. For Free.

# ማውጫ

1. **ዘላለማዊነት**
መለኮታዊነት
ግልጽ ማስገንዘቢዎች
ብሉይ ኪዳን
መለኮታዊ ባህርያት
ሥላሴ
ሥነ ህላዌ
ምጣኔ ሀብታዊ
2. **ተፈጠሮ**
የፍጥረት ሳምንት
የሰው ውድቀት
ግላዊ ውጤቶች
የተበላሸ ህብረት
ጥፋት
ክልከላ
መከራ፣በሽታና ሞት
ጽንፈ ዓለማዊ ውጤቶች
የእግዚአብሔር መንግሥት መዘግየት
ከንቱነት
ለሰብዓዊ ፍጡር ተስፋ
3. **ቤዛነት**
ዓላማ
ሥላሴ
ተፈጥሮ
አማኞች
ተስፋዎች
ሥራ
የመንግሥቱ መምጣት
ታዛዥነት
ትንሣኤ
እርገት

4. **ፍጻሜ**

የኢየሱስ መመለስ
ሁነቶች
  አጠቃላይ ትንሳኤ
  የመጨረሽው ፍርድ
  የተፈጥሮ መታደስ
ውጤቶች
  የእግዚአብሔር ክብር
  የመቤዠት ደስታ

5. **ማጠቃለያ**

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

# 1. መቅድም

የመጫወቻ ጀልባ ስለ ሠራ ትንሽ ልጅ የሚነገር አንድ የቆየ ታሪክ አለ። ልጁ የጀልባውን አካል በጥንቃቄ ቀለም ቀባው፣ የንፋስ መቅዘፊያ ሸራም ሰራለት። ጀልባው ዝግጁ ሲሆን፣አንድ ወንዝ ላይ አንሳፈፈው። ለትንሽ ጊዜ በቀላሉ ተንሳፈፈ፣ግን ብዙም ሳይቆይ በወንዙ ተወሰደ። ልጁ የጠፋ ጀልባውን ፈለገ፣አላገኘውም። ከትንሽ ጊዜ በኋላ፣ትንሽዋን ጀልባውን አንድ እቃ መሸጫ መደብር መስኮት ላይ ስለ አያት ተደነቀ። በፍጥነት ወደ መደብሩ ገባና እንዲህ አለ፣ "ጀልባዬን መስኮቱ ላይ አየሁዋት!"

የመደብሩ ሠራተኛ ግን እንዲህ አለና መለሰለት፣"አዝናለሁ አንተ ልጅ፣ ጀልባውን የምትወስደው ገንዘብ ከፍለህ ነው" ልጁ ጀልባውን እንደገና ለመግዛት የሚያስችለው ገንዘብ ለማገኘት ለሳምንታት ሥራ ሠራ። በዚህ ሁኔታ ጀልባውን ተረክቦ ከመደብሩ በመውጣት ላይ እያለ ለጀልባው እንዲህ አላት፣ "ትንሽዋ ጀልባዬ እንደገና የኔ ሆነሻል። ሠራሁሽ፣ብትጠፊ ፈለኩሽ፣እና ገዛሁሽ"

በብዙ ሁኔታዎች በኢየሱስና በህዝቦቹ መካከል ያለው ግንኙነት፣በትንሹ ልጅና በጀልባው መካከል ያለውን ግንኙነት ይመስላል። የእግዚአብሔር ልጅ ፈጠረን፣ነገር ግን ኀጢአት ውስጥ ገባንና ጠፋን። እርሱ ግን አልረሳንም። የጠፋውን ለፈልግና ሊያድን ወደ ምድር መጣ። ፈልጎ ካገኘን በሁዋላ፣ ሊታደገን ከፍተኛውን ዋጋ ከፈለ-ሞቱን በዋጋነት አቀረበ።

በኢየሱስ እናምናለን በተሰኘው በተከታታዩ ትምህርታችን ውስጥ ይህ የመጀመሪው ሲሆን፣ ሥነ ክርስቶስ፣የክርስቶስ ትምህርት በመባል የሚታወቀውን የስነ መለኮት ከፍል እንመረምራለን። በነዚህ ትምህርቶች ሁሉ፣ተከታዮቹ ስለ ኢየሱስ ሰብእናና ተግባር ለብዙ ሺህ ዓመታት ያረጋገጡዋቸውን ብዙ የተለያዩ አውነቶች እንመረምራለን። ለዚህ የመጀመሪያ ትምህርት የሰጠነው ርእስ፣ "ታዳጊው (ነጻ አውጪው)" የሚል ነው። ይህን ያደረግነው፣ኢየሱስ ለእኛና ለአባቱ ክብር ሲል ኀጢአተኞችን ከኀጢአት ነጻ በሚደርግበትና፣የፍጥረት መጨረሻ ወደ ነበረበት መመለሱን በሚያረጋግጥበት ሁኔታ ላይ ስለምናተኩር ነው።
በዚህ ታዳጊው ኢየሱስ በሚለው ትምህርት፣ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ሰብእናና ስራ በአራት የተለያዩ ክፍሎች እንመረምራለን። መጀመሪያ፣ ከዓለም መፈጠር በፊት፣የእርሱን ነባሪነትና በዘላለም ውስጥ ያለውን እቅድ እንመለከታለን። ሁለተኛ፣በፍጥረት መጀመሪያ ጊዜ የነበረ ሥራውን እንቃኛለን። ሦስተኛ፣ሰው በኀጢአት ከወደቀ በሁዋላ፣ስለ ጀመረውና እስከዛሬ ስለቀጠለው የድነት ዘመን

እንነጋገራለን። አራተኛ፣ኢየሱስ ከተመለሰ በሁዋላ የሚሆነውን የታሪክ ፍጻሜ እንመረምራለን። በዘለዓለም እንጀምር።

## 2. ዘለዓለም

ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች፣ ስለ ክርስቶስ ሰናስብና ስንናገር፣በምድር ላይ በኖረበት ህይወትና አሁን በሰማይ በማድረግ ላይ ባለው ሥራ ላይ እናተኩራለን። እንደውም አንዳንዴ፣ሰለ ኢየሱስ የሚገልጠውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት፣ ወደ ፊት እርሱ በሚመጣበት ጊዜ የሚፈጸም እንደሆነ አድርገን እንገነዘባለን። እነዚህ ሁሉ፣በጣም ጠቃሚ አስተምህሮዎች ናቸው። እውነቱ ግን፣ በኢየሱስ ክርሰቶስነት የምናውቀው፣ ሁለተኛው የስላሴ አካል፣ዘላለማዊ አምላካችን መሆኑ ነው። ስለዚህ፣ ከሥነ መለኮታዊ አተያይ አንጻር ስለ እርሱ በምናስብበት ጊዜ፣ ጌታ በታሪክ ውስጥ ሁሉ፣ ታሪክ ሳይጀመር እንኳዋን፣ድነታችንን ያቅድና ይሠራ እንደነበር ለመረዳት በታሪክ በጣም ወደ ሁዋላ ሄዶ መጀመሩ ብዙ ጊዜ ይረዳል።

የስነ መለኮት ሰዎች፣ከጽንፈ ዓለም መፈጠር በፊት ስለነበረው የዘላለም ሁኔታ ሙሉ በሙሉ አልተስማሙም። እንዳውም አንዳንዶቹ ጊዜ የፍጥረት አንድ ገጽታ ስለሆነ፣ ከእግዚአብሔር የመፍጠር ሥራ በፊት ጊዜ ነበር ብሎ ለመናገር አይቻልም ይላሉ። ስለዚህ በዚህ ትምህርት፣ ዘላለምን ከጽንፈ ዓለም መፈጠር በፊት የእግዚአብሔር ህልውና እንደሆነ አድርገን እንገነዘባለን። በዘለዓለም ውስጥ እግዚአብሔር ብቻ ነው የኖረ። የኖረውም፣ እንደ አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ በስላሴነት ነው።

ስለ ዘለዓለም የምናደርገው ውይይት፣በሦስት ይከፈላል። መጀመሪያ፣ ስለ ክርስቶስ መለኮትነት እና አምላክነት የሚገልጸውን መጽሐፍቅዱሳዊ አስተምህሮ እንመረምራለን። ሁለተኛ፣በስላሴ ውስጥ ያለውን ሚና እንመለከታለን። እና ሦሰተኛ፣ዘለዓለማዊ ምክሩን እንገልጻለን። የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ መለኮትነት እንጀምር።

### መለኮትነት

መጽሐፍ ቅዱስ ጊዜና ታሪክ በነበረበት ወቅት ነው የተጻፈው እንጂ ከዘላለም የመጣ አይደለም። እስከ አዲስ ኪዳን ዘመን ድረስ ኢየሱስን እንደተለየ የስላሴ አካል በግልጽ አያሳይም። ቢሆንም፣ ኢየሱስ በዘለዓለም ሁሉ እግዚአብሔር መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል ያስተምራል። በመሆኑም፣ አዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ መለኮትነቱ የሚገለጡት ነገሮች፣ከጽንፈ ዓለም መፈጠር በፊትም እውነት ናቸው። ስለ እርሱ የተገለጡ እውነቶች ሆነውም ለዘለዓለም ይቀጥላሉ።

*ዕብራውያን ምዕራፍ* 13 ቁጥር 8 ውስጥ እነደምናነበውም፡

> *ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፣ ዛሬም ለዘለዓለምም ያው ነው።* (*ዕብራውያን*13፡8)

የኢየሱስ መለኮትነት አዲስ ኪዳን ውስጥ በብዙ መንገድ ተገልያአል። መጀመሪያ፣ የእግዚአብሔር ቃል እርሱ መለኮት መሆኑን የሚገልጽበት ብዙ ግልጽ ማስገንዘቢያዎች አሉት። ሁለተኛ፣ አንዳንድ የአዲስ ኪዳን ምንባቦች የእርሱን መለኮትነት በሚገልጽ ሁኔታ ብሉይ ኪዳንን ያጣቅሳሉ። ሦስተኛ፣ አንዳንድ ምንባቦች ደግሞ መለኮታዊ ባህርዮችን ይሰጡታል። የኢየሱስን መለኮትነት የሚያረጋግጡትን ምሳሌዎች ከግልጻቹ ማስገንዘቢያዎች በመጀመር እንመለከታቸዋለን።

## ግልጽ ማስገንዘቢያዎች

ብዙ ምንባቦች አርሱን በቀጥታ እንደ እግዚአብሔር በማመልከት ኢየሱስ መለኮት መሆኑን በግልጽ ያስተምራሉ። ለምሳሌ፣ ዮሐንስ ምዕራፍ 20 ቁጥር 28 ውስጥ ሐዋርያው ቶማስ ኢየሱስን “አምላኬ“ ብሎታል። ቲቶ ምዕራፍ 2 ቁጥር 13 ውስጥ፣ ጳውሎስ ኢየሱስን፣ “የታላቁን አምላካችንንና የአዳኛችንን የኢየሱስ ክርስቶስን“ ብሏል። 2ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 ውስጥ፣ ጴጥሮስ ኢየሱስን፣“በአምላካችንና አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ“ ብሎታል። 1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 20 ውስጥ፣ ዮሐንስ ኢየሱስን፣ “እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት“ ብሎታል።

ምናልባት የኢየሱስን መለኮትነት የሚያረጋግጠው ከሁሉ ይልቅ የታወቀው ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 ነው። እንዲህ ይነበባል፣

> *በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፣ቃልም እግዚአብሔር ነበረ (ዮሐንስ 1፡1)*

ይህ ቃል በግልጽ የሚለው፣ቃል እግዚአብሔር ነበር፣ እርሱም አግዚአብሔር ነበር፣ከመጀመሪያ አንስቶ ማለት፣ ጽንፈ ዓለሙ ከመፈጠሩ በፊት፣ እርሱ እግዚአብሔር ነበር፣ ማለት ነው። በዚሁ ምዕራፍ ገባ ብሎ ከቁጠር 14 እስከ 18 ባለው ክፍል የሚናገርለት ቃል ኢየሱስ መሆኑን ዮሐንስ በማያጠራጥር ሁኔታ ገልጧል። እርሱ በማንኛውም መንገድና ሁል ጊዜ ሙሉ በሙሉ መለኮት ነው፣ሆኖም ይኖራል።

### ብሉይ ኪዳን

ሁለተኛ፣ የኢየሱስን እግዚአብሔርነት በግልጽ ከማስገንዘብ በተጨማሪ፣ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ለእግዚአብሔር የሚጠቀሙበትን ቃል አዲስ ኪዳን የኢየሱስን መለኮትነት ለመግለጥ ይጠቀምበታል።

የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች ኢየሱስን ከብሉይ ኪዳኑ ጌታ ጋር እኩል በማድረግ ገልጠውታል። እግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ውስጥ አራሱን ያህዌ፣ በተለምዶ "ጌታ"፣ በሚባለው መጠሪያ ለሕዝቡ፣ ገልጧል። አዲሰ ኪዳን ውስጥም፣ ጸሐፊዎቹ ስለ ያህዌ፣ጌታ፣ በብዙ ቦታዎች በግልጽ የሚያስገነዝቡ ምንባቦች ስለ ኢየሱስ የሚናገሩ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ለምሳሌ፣ማርቆስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 3፣ ሚልኪያስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 1፣ እና ኢሳይያስ 40 ቁጥር 3 ን ይጠቅሳል። ቃላቱ የሚገልጹት፣ አንድ ነብይ ወይም መልእክተኛ በጌታ ፊት የሚሄድ መሆኑን ነው። ማርቆስ ግን እነዚህ ትንቢቶች፣ መጥምቁ ዮሐንስ ለኢየሱስ መንገድ ባዘጋጀለት ጊዜ ተፈጽመዋል ብልዋል። ማርቆስ በዚህ መንገድ ሚልኪያስና ኢሳይያስ የተነበዩለት ኢየሱስ፣ ጌታ፣ ያህዌ መሆኑን አመልክቷል።

ጳውሎስ፣ ኢየሱስ ጌታ የመሆኑን መሠረታዊ አዋጅ በገለጸበት ፊልጵስዩስ ምዕራፍ 2 ቁጠር 11 ውስጥ በኢየሱስና በያህዌ መካከል ያለውን ተመሳሳይ አንድነት ገልፆአል። ዮሐንስ ምእራፍ 1 ከቁጥር 1-3 ባለው ክፍልም ኢየሱስ እግዚአብሔር በመጀመሪያ በእርሱ በኩል ጽንፈ ዓለሙን የፈጠረበት የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ዮሐንስ ያመለክታል። ይህ፣ ሙሴ፣ "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ" በማለት የገለጠበት የዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 ግልጽ ጥቅስ ነው። ይህ የኢየሱስን በመፍጠር ሥራ መሳተፍ የሚገልጽ ጥቅስ፣ እርሱ በእርግጥ አግዚአብሔር መሆኑን ያመለክታል።

### መለኮታዊ ባህርያት

ሦስተኛ፣ ኢየሱስ እግዚአብሔር መሆኑን ለማረጋገጥ፣ በግልጽ መግለጫዋች እና በብሉይ ኪዳን ከመጠቀም በተጨማሪ፣ የአዲስ ኪዳን ጸሀፊዎችም ለኢየሱስ የመለኮታዊነት ባህርያትን ሰጥተውታል፣ ማለትም እግዚአብሔር ብቻ ሊኖሩት የሚቻለውን ባህርያት ማለት ነው።

ለምሳሌ፣ ዕብራውያን ምዕራፍ 1 ቁጥር 3 እንዲህ ይላል፣

*እርሱ የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅና የባህርዩ ትክክለኛ ምሳሌ ሆኖ፣ በሀያል ቃሉ ሁሉን ደግፎ ይዞአል፣የሀጢአት መንጻት ካስገኘ በሁዋላ፣ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ።*

እዚህ ላይ የወልድን መለኮትነት በሚያመለክት መንገድ፣ ወልድ ከእግዚአብሔርና ከክብሩ ጋር ተስተካክሎ ቀርቧል። ከሁሉም ይበልጥ፣ ወልድ ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር የመፍጠርና የማኖር ሃይል ይዟል። ውሱን ያልሆነው እግዚአብሔር አንጂ፣ማንም ውሱን የሆነ ፍጡር የማይወሰን ሀይል ሊኖረው አይችልም። ስለዚህ፣ ወልድ ራሱ እግዚአብሔር መሆን አለበት።

ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እና 2፣ ቀጥሎ ያለውን ቃል በሚገልጥበት ጊዜ፣የኢየሱስን መለኮትነት በተመሳሳይ መንገድ ያረጋግጣል፣

> "በመጀመሪያ ቃል ነበረ...እርሱም በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ" (ዮሐንስ1፡1-2)

ዮሐንስ "በመጀመሪያ" ቃል ነበረ በሚልበት ጊዜ፣ ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እግዚአብሔር ከፍጥረት በፊት ለዘላለም መኖሩን እንደሚያስተምር፣ ወልድም ዓለም ከመፈጠሩ እና ከዘላለም በፊት፣ምንም ሳይፈጠር ነበር ማለቱ ነው። በሌላ አነጋገር፣ ወልድ ፈጡር አይደለም፣ በዘላለም ሁሉ ከአብ ጋር ኖሯል። ለዘላለም የመኖር ባህርይ ያለው እግዚአብሔር ብቻ ሰለሆነ፣ወልድ እግዚአብሔር ራሱ መሆን አለበት።

ክርሰቶስ ሙሉ መለኮትነት ያለው መሆኑን ካየን እንግዲህ፣ በወልድ እና በሌሎቹ የስላሴ አካላት መካከል ወዳለው ግንኙነት ዞር ለማለት ዝግጁ ነን።

## ሥላሴ

ትምህርተ ሥላሴ ለክርስተና ትምህርት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። በሌላ በኩል፣ትምህርተ ሥላሴ፣ እግዚአብሔር ልንረዳው ከሚቻለን አቅም በላይ መሆኑን ከሚያስተምሩን አስተምህሮዎች አንዱ ነው። እግዚአብሔር ሚስጢራዊ እና ተዓምራዊ መሆኑን እያስተማረም ያነሳሳናል። በሌላ በኩል ግን፣ይህ አስተምህሮ ክርስትናን ከሌሎች ሀይማኖቶች ሁሉ የተለየ ያደርገዋል። አንዳንድ ሀማኖቶች እግዚአብሔርን በቀላሉ እንደ አንድ አካል ሲመለከቱት እና፣ ሌሎቹ በዙ ሌሎች እግዚአብሔሮች አሉ ብለው ሲያምኑ፣ስለ ሥላሴ የሚገልጸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ

ግን፣እግዚአብሔር በአንድ ግንዛቤ ሦስት፣ በሌላው አንድ መሆኑን ያስተምረናል። ይህ ልዩ ክርስቲያናዊ አስተምህሮ፣ በታሪክ ሂደት ስለ ክርስቶስ ያለን እምነት መሠረት ነው።

ሥላሴ የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይኖርም፣እግዚአብሔር በአካል ሦስት፣ በባህይ ግን አንድ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። አካል የሚለው ቃል ልዩ እና የራሱ ግንዛቤ ስለ አለው አካል ነው የሚያመለክተው። ሦስቱ የእግዚአብሔር አካላት፣ አብ፣ ወልድ፣ እና መንፈስ ቅዱስ መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል። ባህርይ የሚለው ቃል ደግሞ፣የእግዚአብሔርን መሠረታዊ ምንነት ያስረዳል።

> *ስለ ሥላሴ የሚገልጸው ክርስቲያናዊ አስተምህሮ፣ አንድ እግዚአብሔር በሦስት አካላት በህብረት፣እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሆኖ በዘላለማዊነት እንደሚኖር ይገልጻል። እግዚአብሔርን በተመለከተ እንዲህ ካለው ግንዛቤ ላይ ለመድረስ፣ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በመታገል ብዙ ምዕተ ዓመታት ወስዶባቸዋል። ለሥላሴ አስተምህሮ እድገት ዋነኛውን ሚና የተጫወተው፣ የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች ከሞት የተነሳውንና ከፍ ከፍ ያለውን ክርስቶስ ማምለካቸው…ኢየሱስ መለኮት መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ማስተማሩ ነው። ይህን የገለጹት፣ወልድ ከአብ ጋር በባህርይ አንድ ነው በማለት ነበር። ታዲያ ክርስቲያኖች ክርስቶስን ማምለክን ከእግዚአብሔር አንድ መሆን ጋር የሚያስታርቁት እንዴት ነው? ቁልፉ ልዩነት፣ በአካልና በፍጥረት መካከል ያለው ነው። በመጨረሽም ክርስቲያኖች እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔር ወልድ በህልውና አንድ፣ በአካል ግን የተለያዩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ነበር የተመሩት። ለማጠቃለል፣ አንድ እግዚአብሔር እንደ ሦስት አካላት ህብረት ሆኖ ለዘለዓለም ይኖራል፣ ያም አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ሆኖ ማለት ነው። (ዶክተር ኪት ጆንሰን)*

ሥነ መለኮታውያን ስላሴን በተመሳሳይ ሁኔታ ከሁለት እይታ አንጻር ገልጸዋል። በአንድ በኩል በሥላሴ አካላት መካከል ያለውን ግንኙነት ሥነ ህላዌ በሆኑ መንገዶች አስገንዝበዋል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ስለ የሥራ ድርሻ ግንኙነቶች ተናግረዋል። በሥነ ህላዌ ግንኙነቶች በመጀመር እነዚህን ሁለት ሀሳቦች በአጭሩ እንመለከታቸዋለን።

## *ሥነ ህላዌነት*

ህልው መሆን ማለት ከህልውና ጋር መገናኘት ማለት ነው። በመሆኑም፣ በሥላሴ አካላት መካከል ያለውን ሥነህላዌያዊ ግንኙነቶች በምንመለከትበት ጊዜ፣አርስ በእርሳቸው የተዋሀዱበትን እና አንድ መለኮታዊ ባህርይ የተጋሩበትን ሁኔታ ለማወቅ መጓጓታችን ነው። ሦስቱም የእግዚአብሔር አካላት አንዱን መለኮታዊ ባህርይ ስለሚጋሩ፣ውሱን ያለመሆን፣ ዘለዓለማዊነት እና ያለመለወጥን የመሰለ አንድ ባህርይ አላቸው።

ፊልጵስዩስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 5-8 ባለው ክፍል፣ ጳውሎስ ሥላሴን በተመለከተ እንዲህ ብሏል፣

> *በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ በእናንተም ዘንድ ይሁን፤ እርሱ በባህርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊለቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቆጠረውም፤ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም አምሳል ተገኝቶ ራሱን ባዶ አደረገ፣ ሰው ሆኖ ተገልጦም ራሱን ባዶ አደረገ፣እስከ ሞት፣ ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ (ፊልጵስዩስ 2፡5-8)*

ይህ ምንባብ ስለ ኢየሱስ ብዙ ነገሮችን ይናገራል። ልናተኩር የምንፈልገው ግን "በባህርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ" በሚለው አንቀጽ ላይ ነው። በዚህ አንቀጽ፣ጳውሎስ ወልድ የመለኮት ባህርይን ወይም መለኮትነትን ከእግዚአብሔር አብ ጋር የሚጋራ መሆኑን በግልጽ አስተምሯል። ሌሎቹ ምንባቦችም ይህ ገለጻ ለመንፈስ ቅዱስም እውነት መሆኑን ያመለክታሉ። ሦስቱም መለኮት ናቸው።

> ኢየሱስ በዮሐንስ ምዕራፍ 10 ቁጥር 30 ውስጥ እንዲህ ብልዋል፡
> *"እኔና አብ አንድ ነን"* (ዮሐንስ 10፡30)

ኢየሱስ ይህን አስገራሚ መግለጫ ሲናገር የሰሙ ኢአማኒያን አግዚአብሔር ነኝ ማለቱን ተረድተው፣ እግዚአብሔርን ተሳድቧል በሚል ሊወግሩት መከሩ።

ስለ ሥላሴ ሥነ ህለዌ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን አሰተምህሮ ከተመለከትን እንግዲህ፣በሥላሴ ውስጥ ስለ አለው የተግባር ግንኙነት የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረውን እንመልከት።

*የሥራ ግንኙነት*

የ "*የሥራ ግንኙነት*" ትርጉም፣ ከቤተሰብ አስተዳደር ጋር ይዛመዳል:: በመሆኑም በሥላሴ መካከል ስለ አለው የሥራ ግንኙነት በምንነጋገርበት ጊዜ፣አብ፣ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደሚገናኙና፣ እንደ ተለያዩ አከላትነትቸው እንዴት እርስ በርሳቸው እንደሚሠሩ ለመረዳት መሻታችን ነው::

ከሥነ ህላዌ አንጻር እንደተመለከትነው፣ ወልድ ከአብ እና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ የሆነ መለኮታዊ ማንነት አለው:: በአሠራር ግንኙነታቸው ግን፣ወልድ ለአብ ፈቃድ የሚገዛ ሲሆን፣ በመንፈስቅዱስ ላይ ሥልጣን አለው::

ኢየሱስ በዮሐንስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 38 ውስጥ እንደተናገረው፡

*"ከሰማይ የመጣሁት የራሴን ፈቃድ ለማድረግ ሳይሆን፣ የላከኝን የእርሱን ፈቃድ ለማድረግ ነው" (ዮሐንስ 6፡38)*

በዮሐንስ ምዕራፍ 8 ቁጥር 28 አና 29 ውስጥም እንዲህ ብሏል፣

*"አብ ያስተማረኝን እንደምናገር፣በራሴም ፈቃድ ምንም እንደማላደርግ፣ታውቃላችሁ፣*

*የላከኝ እርሱ ከእኔ ጋር ነው፣ምን ጊዜም የሚያስደስተውን ስለማደርግ፣ብቻዬን አልተወኝም::" (የሐንስ 8፡28-29)*

በሥላሴ አሠራር ውስጥ፣ ወልድ ሁልጊዜ ለአብ ሥልጣንና ፈቃድ ይታዘዛል:: አብ በወልድ ላይ ሥልጣን እንዳለው ሁሉ፣ አብ እና ወልድ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ሥልጣን አላቸው::

ወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ሥልጣን ያለው መሆኑን ዮሐንስ 15 ቁጥር 26 ውስጥ እንዲህ በማለት ተናግርዋል፣

*"እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ከአብ የሚመጣው አጽናኙ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለእኔ ይመሰክራል" (ዮሓንስ 15፡26)*

አብ ወልድን ለመላክ ሥልጣን እንዳለው፣ወልድም መንፈስ ቅዱስን ለመላክ ሥልጣን አለው::

በሥላሴ መካከል ምንም ዓይነት ግጭት ተፈጥሮ አያውቅም:: አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ሁል ጊዜ ይስማማሉ:: አንድ አዕምሮ ነው ያላቸው:: ይህም ቢሆን፣ በአሠራረር ግንኙነታቸው ውስጥ ግልጽ የማዕረግ ቅደም ተከተል አለ፣ አብ ከፍተኛውን ሥልጣን፣ከዚያ ወልድ፣ በመጨረሻ መንፈስ ቅዱስ::

የሥላሴን ባህርይ እና፣ በውስጣቸው ያሉ አካላትን ግንኙነት መረዳቱ የሚቻለን አይደለም:: የእግዚአብሔር ቃል የሚገልጸው ነገር እውነት መሆኑን በእምነት እናውቃለን:: ነገር ግን፣ የሥላሴ ብዙ ነገሮች ከመረዳት አቅማችን በላይ መሆናቸውን ማመን አለብን:: ቢሆንም፣ ሁሉም የሥላሴ አካላት ድነትን ሊያስገኙልን አብረው የሚሠሩ መሆናቸውን በማመን ደስ ሊለንና ልንበረታታ እንችላለን:: ወልድ በፈጸመው የቤዛነት ሥራ ላይ በመመሥረት አብ ይቅርታ ያደርግልናል:: አብ እና ወልድ በአንድነት ደግሞ፣ንስሐ እንድንገባና ወልድ ድነታችንን ፍጹም ለማድረግ እስኪመጣ ድረስ ህይወታችንን እንዲያድስ መንፈስ ቅዱስን ይልኩልናል::

መለኮትነቱን እና በሥላሴ ውስጥ ያለውን ሚና አይተን፣ኢየሱስ በዘላለም ውስጥ ያለውን ሥራ እና አካልነቱን መርምረናል:: ስለዚህ ወደ ዘለዓለማዊ ድንጋጌው እንመለስ::

**መለኮታዊ ውሳኔ (አስተዳደር)**

ዘላለማዊ ምክር የሚለው ሥነ መለኮታዊ ቃል፣ ብዙ ጊዜ "ዘላለማዊ ውሳኔ" ፣እግዚአብሔር ከመፍጠር ሥራው በፊት ለጽንፈ ዓለሙ የወሰናቸውን እቅዶች ያመለክታል:: የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ውሳኔ፣እንደ ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ቁጥር 23፣ ሮሜ ምዐራፍ 8 ከቁጥር 28-30፣እና 1ጴጥሮስ ምዕራፍ1 ቁጥር 2 ውስጥ ተጠቅሰዋል::

የተለያዩ ሥነ መኮታዊ ባህሎች የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ እቅድ መጠን በተመለከተ የተለያዩ እምነቶች አሉዋቸው:: አንዳንዶች፣የእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ ማንኛውንም የታሪክ ዝርዝር ነገር ያካትታል ይላሉ:: ሌሎቹ ደግሞ እግዚአብሔር አንዳንድ ነገሮችን እንጂ፣ ሌሎቹን አልወሰነም ብለው የምናሉ:: ክርስቶስ የፈጸመው ሥራ ለእግዚአብሔር ዕቅድ ማዕከል ስለመሆኑ፣ እግዚአብሔር ድነት በእርሱ በኩል እንዲሆን መወሰኑን እና ክርስቶስም እንደሚያከናውነው ሁላችንም እንስማማለን::

ኤፌሶን ምዕራፍ 1 ቁጥር 4 እና 11 እንደምናነበው፣

"በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በእርሱ መርጦናል፣...ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሰረት እንደሚሠራው እንደ እርሱ ዕቅድ አስቀድሞ የተወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል"(ኤፌሶን 1፡ 4 እና 11)

እግዚአብሔር በክርስቶስ ያደረገው፣ድንገተኛ ነገር ወይም የአንድ ያልተወቀ ችግር ማስተካከያ አልነበረም። በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ውሳኔ መሠረት የሆነ ነበር። ክርስቶስን በተመለከተ ስለ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ውሳኔ በምናስብበት ጊዜ፣ ሁለት ነገሮችን መለየቱ ይረዳል፣ቀድሞ ማወቅ እና ዓላማ።

እነዚህ ሁለት የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ውሳኔ ገጽታዎች ምስክር የሆኑበት አንድ ምንባብ ኢሳይያስ ምዕራፍ 46 ቁጥር 10 ነው። በዚያ ስፍራ እግዚአብሐር የተናገረውን አድምጡ፣

*"የመጨረሻውን ከመጀመሪያው፣ገና የሚመጣውንም ከጥንቱ ተናገርያለሁ፣ዐላማዬ የጸና ነው፣ደስ የሚያሰኘኝንም አደርጋለሁ እላለሁ"(ኢሳይያስ 46፡10)*

የእርሱን አስቀድሞ ማወቅ በተመለከተ እግዚአብሔር ከመጀመሪያው፣ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት ማለት ነው፣ገና የሚመጣውን ያውቅ እንደነበር ተናግሯል። ዓላማውን በተመለከተም እንዲህ ብሏል፣"ዓላማዬ የጸና ነው፣ደስ የሚያሰኘኝንም አደርጋለሁ"

እነዚህን ሁለት ሀሳቦች ትንሽ ዘርዘር አድርገን እንመልከታቸው።

አስቀድሞ ማወቅ የሚለውን ቃል፣በአንድ በኩል፣ከፍጥረት በፊት፣ በታሪክ ሂደት የሚሆኑትን ነገሮች እግዚአብሔር ስለ ማወቁ ይገልጣል በማለት እንናገር ይሆናል። አብ፣ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ሁሉን አዋቂ ናቸው። እውቀታቸው እስከ ወደፊቱ እንኳን የሰፋ ነው። ይህን ሀሳብ ከመመልከት በተጨማሪ፣ ኢሳይያስ ምዕራፍ 46 ቁጥር 10፣ ምዕራፍ 42 ቁጠር 9፣ ምዕራፍ 45 ከቁጥር 11-13፣ እና ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ቁጥር 17 እና18ን ማየት ይቻላል።

በሌላ በኩል፣እግዚአብሔር ጽንፈ ዓለሙን የፈጠረበት ዓላማ በብዙ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል። በዚህ ትምህርት፣ እግዚአብሔር ጽንፈ ዓለሙን የፈጠረው፣ በክርስቶስ በሚሆነው መንግሥቱ በኩል ክብሩን ለመግለጽና ለመጨመር ነው፣በማለት እናሳጥረዋለን። ይህ ዓላማው እግዚአብሔር ቃል ውስጥ፣ መዝሙር 145 ከቁጥር 1-21፣ 1 ጢሞቲዎስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 17፣ ዕብራውያን ምዕራፍ 1 ከቁጥር 1-13፣1 ጴጥሮስ

*ምዕራፍ*1 ከቁጥር 20 እስከ *ምዕራፍ* 2 ቁጥር 9፣ *ራዕይ ምዕራፍ* 1 ቁጥር 5 እና 6 ውስጥ ተገልጾ እናያለን።

> *በቅርብ ዐሥርተ ዓመታት አንዳንድ ሥነ መለኮታውያን፣ የእግዚአብሔርን የከበረ መንግሥት በተመለከተ፣ ዘላለማዊ ውሳኔውን ወይም ድንጋጌውን እንደ ቃል ኪዳናዊ መቤዠት መግለጡ የሚረዳ መሆኑን ተረድተዋል። እግዘአብሔር አብ፣ከዓለም መፈጠር በፊት መቤዠትን አስተማማኝ ለማድረግና ለወደቀው ተፈጥሮ ለማዋል ወደ ብርቱ ማደራጀት መግባቱን መጽሐፍ ቅዱስ ያመለክታል። በተለይ ወልድ የወደቀውን ሰብዓዊ ፍጡር ከኀጢአት ፍርድ ለማዳን ሲል ሥጋ ለመልበስና ለመሞት ተስፋን ሰጠ። አብም የወልድን ለኀጢአተኞች መቤዠት የሚቀርብ መሰዋዕተነት ለመቀበል ተስፋን ሰጠ። አንዳንድ ሥነ መለኮታውያን መንፈስ ቅዱስ ድነትን ለተዋጁ ኀጢአተኞች እንዲደርስ የሰጠውን ተስፋም ይጨምራሉ።*
>
> *ይህ፣ አብ ለሕዝቡ ሲል የድነትን ሥራ የሚያቅድበት ስምምነት ነበር። ወልድ መጥቶ ሥጋ የሚለብስበትን አካል ለወልድ እንደሚሰጥም ይወስናል። ወልድም ወደዚህ ዓለም መጥቶ ህይወቱን፣ ፍጹም የሆነ ህይወት- ያን ፍጹም ህይወት በመስቀል ላይ ለመስጠትና ለእግዚአብሔር ሰዎች ምትክ ለመሆን ይስማማል። የድነት ቃል ኪዳኑ ሌላ ክፍል ደግሞ፣ የክርሰቶስን ሥራ በመውሰድ ለእግዚአብሐአር ሕዝብ የሚያደርሰውን መንፈስ ቅዱስ መላክ ነው።(ዶክተር ጂፍ ሎውማን)*

ኢየሱስ ያደረጋቸውንና በሥጋ ሆኖ የሚያደርጋቸውን ስለሚገልጽና በአጭሩ ስለሚያስረዳ፣ የድነት ቃል ኪዳንን መረዳታችን ለግንዛቤያችን ጠቃሚ ነው። በድነት ቃል ኪዳን ውስጥ ያሉ ተስፋዎች፣ እንደ መዝሙር 110፣እና ኤፌሶን *ምዕራፍ* 1 ቁጥር 3-6 ውስጥ ተጠቅሷል። እንደ 1 ጴጥሮስ *ምዕራፍ* 1 ቁጥር 20 እና *ራዕይ ምዕራፍ* 13 ቁጥር 8 ባሉት ሥፍራዎችም መኖራቸው ይታወቃል።

እንደ አንድ ምሳሌ ኢየሱስ ዮሐንስ *ምዕራፍ* 6 ከቁጥር 38-40 የተናገራቸውን ቃላት አድምጡ፣

> *"ከሰማይ የወረድሁት የራሴን ፈቃድ ለማድረግ ሳይሆን፣ የላከኝን የእርሱን ፈቃድ ለመፈጸም ነውና፣የላከኝም ፈቃድ ከሰጠኝ ሁሉ አንድ እንኳን ሳይጠፋብኝ በመጨረሻ ቀን እንዳስነሳ ነው። የአባቴ ፈቃድ ወልድን አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው ነው፣ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሳዋለሁ" (ዮሐንስ 6፡38)*

*ድነት፣ከዓለም መፈጠር በፊት በእግዚአብሔር ውስጥ የነበረና ከአንድ ዘላለማዊ ቃል ኪዳን ጋር የተገናኘ ጉዳይ ነው። የዚህን ምስጢሮች በትክክል ለመግለጽ አንችልም። አግዚአብሔር ፍጹም መሆኑ፣አንዳንድ ነገሮች ከእኛ የተደበቁ መሆናቸው እና አግዚአብሔርም ያልገለጻቸው መሆኑ ይታወቃል። ነገር ግን፣ እግዚአብሔር ሰለዚህ ነገር የገለጻቸውን ሁሉ ለመረዳት እንፈልጋለን፣ የክብሩ መገለጫ በዘላለምና በሥላሴ ውሰጥ የነበረ ቃል ኪዳን መሆኑን በመላው መጽሐፍ ቀዱስ እናነባለን። በመሆኑም ከእግዚአብሕር ሌላ የሆኑ ፍጡሮች በክብሩ ይደሰታሉ፣ የሚጨምርና ፍጻሜ የሌለው ደስታም ይሆናል። ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንመለከተው፣ እግዚአብሔር ይህን የሚያደርግበት መንገድ በመታደግ ዓላማ በኩል ይመስላል። ቅጣት የሚገባቸውን ሰብዓዊ ፍጡራን ለመቀበልና ለመታደግ። ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው፣ ዓለም ከመመሥረትዋ በፊት፣ዓለም ከመፈጠርዋ በፊት፣ አብ አንድ ሕዝብ የሚመርጥበት፣ወልድ መጥቶ የሚሞትበትና ሕዝብን የሚታደግበት፣ ከዚያም መንፈስ ቅዱስ የኀጢአት ርኩሰትን ከእነርሱ በማስወገድ ንስሀ እንዲገቡና ኢየሱሰን እንዲቀበሉ ሕዝብን እንዲያያከማች ይህ ማዘጋጀት ተከናወነ። (ዶክተር ቶማሰ ኔተልስ)*

የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ምክር ወይም ውሳኔ፣ ለአማኞች ሁሉ አስገራሚ የበረከት ምንጭ ነው። አግዚአብሔር ጽንፈ ዓለሙን ከመፍጠሩ በፊት ክብሩን ለመግለጽ እና በቸርነቱ ስር ለሚኖሩ ሰብዓዊ ፍጡራን መኖሪያነት ተሥማሚ እንዲሆን ተፈጥሮን አቀደ። ከቀዳሚ አዋቂነቱ የተነሣ ምንም አያስደንቀውም። በሰው በኀጢአት መውደቅ እግዚአብሔር አልደነገጠም። ድነታችንም አንድን ድንገት የተሰበረ ነገር ለመጠገን የተደረገ የመጨረሽ ደቂቃ ሙከራው አይደለም። በተቃራኒው ሁሉ ነገር እንደ እቅዱ ይሆናል። አስደናቂ ቢመስልም፣ እግዚአብሔር ራሱ፣ የጽንፈ ዓለሙ መሀንዲስና ፈጣሪ፣ እንደ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆኖ ሥጋ ለበሰ። በዘላለማዊ ዓላማው መሠረት ተፈጥሮን እንደገና ወደ ነበረበት ለመመለስ ፈጠረ፣እኛንም።

## 3 ፍጥረት

በዚህ ትምህርት ውስጥ ላለን ዓላማ፣ የፍጥረትን መጀመሪያ ጊዜ፣በፍጥረት ሳምንት ጀምሮ፣ በሰው በኀጢአት መውደቅ እና ከኤደን ገነት መባረር እንዳበቃ እንገልጻለን። እነዚህ ሁነቶች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሰዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገለጹባቸው ዋና ስፍራ ግን፣ዘፍጥረት ከምዕራፍ 1-3 ያለው ክፍል ነው።

ሁለት አርእስትን በመመልከት፣በፍጥረት ጊዜ የወልድን *ሥራ* እናጠናለን። መጀመሪያ፣ እግዚአብሔር ጽንፈ ዓለሙን የፈጠረበት ጊዜ፤ እና ሁለተኛ፣ የሰው ኀጢአት ውስጥ መውደቅ። በፍጥረት ሳምንት እንጀምር።

**የፍጥረት ሳምንት**

ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ዓለምን ስለ መፍጠሩ በሚናገሩበት ጊዜ፣አእምሯችን በተለምዶ ወደ እግዚአብሔር አብ ይሄዳል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን ግን፣በፍጥረት ጊዜ ወልድ በአብ ጎን ነበር፣ አብም ዓለምን በእርሱ ወይም በእርሱ አማካይነት ነው የፈጠረው። እነዚህ እውነቶች፣ ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 1-3 እና ዕብራውያን ምዕራፍ 1 ቁጥር 2 በመሳሰሉ *ሥፍራዎች* ትምህርት ተሰጥቶባቸዋል።

> *እግዚአብሔር ወልድ የጽንፈ አለሙ ፈጣሪ ስለ መሆኑ በምናስብበት ጊዜ፣ ወደ አእምሮዋችን የሚመጣው ምንባብ፣ ሙሉ የሆነው ቆላስያስ መእራፍ 1 ሲሆን፣ነገሮች ሁሉ በእርሱ መፈጠራቸውን፣ሁሉም በአንድ ላይ ተያይዞ የጸናው በእርሱ መሆኑን፣ለእርሱ እንደተሠሩ፣ይህም ወደ እውነተኛ ተግባራዊነት እንደሚደርስ ያስታውሰናል። ይህ የሚያስገነዝበን፣ይህን ፍጥረት ያቀደና ቅርጽ የሰጠ፣በተፈጥሮ ህግ እና በመለኮታዊ ፈቃዱ የሚጠብቅ፣ እዚህ በምድር ላይ፣ እንደ የተፈጥሮ አካልነታችንና በመንፈሱ የተፈጠርን እንደ መሆናችን የምናልፍበትን ሁኔታ የሚያውቅ ስለ መሆኑ እርግጠኞች መሆን እንደምንችል ነው። ስለዚህ፣ ዛሬ ከእግዚአብሔር የመጀመሪያ ዓላማ እና መልካምነት ጋር የሚያያዝ በረከት አለ።*(ዶክተር ዲ.ስሚዝ)

ለምሳሌ፣ ቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጠር 16 በፍጥረት ውስጥ ስለ ወልድ ተሳትፎ የሚለውን ስሙ፣

> *"ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፣ በሰማይና በምድር ያሉ የሚታዩና የማይታዩ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ሀይላት፣ ገዦች ቢሆኑ ወይም ባለሥልጣናት፣ ሁሉም ነገር በእርሱና ለእርሱ ተፈትሮአል"*
> *(ቆላስይሰ 1:16)*

በዚህ ምንባብ ውስጥ፣ ጳውሎስ፣ ተፈጥሮ በወልድ፣ወይም አንዳንድ ትርጉሞች እንደሚገልጡት በእርሱ "በኩል" ተከናውንዋል በማለት በግልጽ ተናግርዋል።

*በፍጥረት ጀመሪያ ወልድ እንደ ሎጎስ፣እውነተኛ ቃል ሆኖ ነው የቀረበው። በመሆኑም ዘፍጥረት 1 ውስጥ፣ እግዚአብሔር "ብርሀን ይሁን" አለ። እንዲሁም "ውሆች ይሰብሰቡ፣ ደረቅ ምደር ይታይ" አለ። ከዚያም ዮሐንስ በወንጌሉ ውሰጥ "ቃል ሥጋ ሆነ" አለ። በመሆኑም፣ ጽንፈ ዓለሙን የምንመለከተው፣በተመሳሳይ መንገድ ነው፣ከፈጣሪ እስከ ፍጥረት፣ ከሰው እስከ ሰብዓዊ ፍጡር። ለምን? ምክንያቱም ዓለምን የምንረዳው፣በእግዚአብሔር ገዢ መርህ ነው። መርሁ ደግሞ ሀሳባዊ አይደለም፤እውነት ነው፣ ቃል፣ ሎጎስ። በዚህ ሁኔታ ጽንፈዓለሙ በእግዚአብሔር ቃል፣ ሎጎስ፣ የሚገዛ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል።(ዶክተር ስቲፈን ቻን)*

*ታውቃላችሁ፣ አዲስ ኪዳንን በምናነብበት ጊዜ ብዙ የሚያስደንቁ ነገሮች አናገኛለን፣ እናም ብሉይ ኪዳንን ሙሉ በሆነ ብርሃን እናነበዋለን። ዮሐንስ ወንጌል መግቢያ ላይ ከምናገኘው ነገር አንዱ፣ለምሳሌ፣ ክርስቶስ ከመጀመሪያ አንስቶ መኖሩን ነው። እርሱ በእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሰረት የብሉይ ኪዳን ነው። ነገር ግን ወደ ሁዋላ እስከ ዘፍጥረት መጀመሪያ እንሄድና እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው፣ ቃል በሆነው በክርስቶስ፣ በሎጎስ መሆኑን ዮሐንስ ይነግረናል። ከዚያም የቆላስያስን መልእክት ወደ መሰለው ስፍራ ስንሄድ፣ ወልድ ዓለምን መፍጠር ብቻ ሳይሆን፣ሁሉን ወደ መኖር ያመጣውም እርሱ መሆኑን ጳውሎስ ይነግረናል። ፍጥረት የቃል መሆኑን እግዚአብሔር እንደተናገረም ዘፍጠረት ገልጾልናል። እግዚአብሔር የተናገረበት ቃል ነበር። ያ ቃል ክርስቶስ መሆኑን ወደ መገንዘብ እንደርሳለን።(ዶክተር አር.አልበርት ጀ. አር)*

ደስ ሚለው ነገር፣መጽሐፍ ቅዱስ ስለፍጥረት የሚገልጸው ትረካ የሚጀምረው፣ ከሰማያትና ከምድር መፈጠር በፊት በሆነው ነገር ላይ በማትኮር አይደለም። ከዚያ ይልቅ፣ ብዙውን ጊዜ የሚወስደው፣ እግዚአብሔር ደስ በሚለው መንገድ፣ በትእዛዙ፣ ዓለምን ስለሞላበትና ለጽንፈ ዓለሙ ባለው እቅድ በሚስማማ መንገድ ማከናወኑን በመግለጽ ነው። ዘፍጥረት ምእራፍ 1 ቁጥር 2 በጣም ስለቀደመው ዓለም ሁኔታ ይነግረናል። ጥቅሱ እንዲህ ይላል ፣

*ምድር ቅርጽ የለሽና ባዶ ነበረች። የምድርን ጥልቅ ሥፍራ ሁሉ ጨለማ ውጦት ነበር (ዘፍጥረት 1፡2)።*

እግዚአብሔር ከማዘዙና ከመሙላቱ በፊት፣ ጽንፈ ዓለሙ ምንም ቅርጽ ወይም ሥርዓት ያልነበረው ቅርጸቢስ ነበር፣ምንም ፍጡር የማይኖርበትና ባዶ።

በዚህ ሁኔታ ዓለም በክብር የተሞላ የእግዚአብሔር መንግሥት ለመሆን ተስማሚ አልነበረም። በመሆኑም እግዚአብሔር የፈጠረውን ዓለም በመሙላትና ፍጥረቱን ሥርዓት በማስያዝ ስድስት ቀናት አሳለፈ። ይህን ያደረገበት መንገድ፣ ለዓለም ያለውን ዘላለማዊ ዓላማ አንዳንድ መሰረታዊ አቅጣጫዎች ገልያአል።

በመጀመሪያዎቹ ሦስት የፍጠረት ቀናት ውስጥ፣ እግዚአብሔር መንግሥቱ ሥርዓት እንዲይዝና እዲገዛለት ባዶውን ዓለም ሞላው። ወቅቶችን ለመለየትም ጸሀይን፣ ጨረቃንና ከዋክብተን ፈጠረ። ጸሀይ ቀኑን እንድትመራ ወይም እንድትገዛ፣ጨረቃ ደግሞ ሌሊቱን እንድትገዛ አደረገ። ውቅያኖስ ውስጥ እንዲኖሩ አሳንና ሌሎች የባሕር ፍጡራንን ፈጠረ፣ በሰማይ የሚኖሩ አእዋፍን ሠራ፣ በምድር የሚኖሩና ደረቂቱን መሬት የሚሞሉ እንስሳትን ፈጠረ። ከዚያም ምድርን እንዲሞላትና የባሕርን፣የሰማይንና የምድርን ፍጡራን ሁሉ እንዲገዛ ሰውን ፈጠረ።

ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 27 እና 28 ውስጥ የተጠቀሰውን የሰው አፈጣጠር መግለጫ ተመልከቱ፣

> *"ስለዚህ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ ፈጠረው፣በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው። እግዚአብሔርም ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉዋት፣ ግዙዋትም የባሕርን አሶች፣የሰማይን ወፎች፣ እንዲሁም በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ህያዋን ፍጡራንን ሁሉ ግዙዋቸው ብሎ ባረካቸው" (ዘፍ. 1፡ 27-28)*

> *ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው የመጀመሪያ ግንኙነት እንዲህ በሰፊው የተገለጸ እንደነበር የእግዚአብሔር ቃል፣ በተለይም የዘፍጥረት መጽሐፍ ይነግረናል። ከሁሉ በፊት፣ሰብዓዊ ፍጡራን፣የእግዚአብሔር ፍጥረት ፍጹም አናት ናቸው። በስድስተኛው ቀን ፍጻሜ፣እግዚአብሔር፣"… ሰውን በራሱ መልክ ፈጠረው፣ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው"። ስለዚህ ሰብዓዊ ፍጡራን በዚህ ፍጥረት ውስጥ እንዲህ አናትነትን የመሰለ፣እግዚአብሔር ሊሠራ የፈለጋቸው ነገሮች ሁሉ መደምደሚያ፣የምስሉ ሥፍራ፣አምሳያው የመሆን ግንኙነት አላቸው። ሁለተኛው የዘፍጥረት ምዕራፍም፣እግዚአብሔር አዳምን ከምድር አፈር ሰርቶት ህይወትን እፍ እንዳለበት፣መለኮታዊ ህይወቱን ለአዳም አንዳካፈለው ያንኑ እውነት በዚህ መልኩ ይገልጻል። ስለዚህ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው የመጀመሪያ ግነኙነት ምናልባት በነዚህ አባባሎች ከሁሉ በላቀ ሁኔታ ተገልጽዋል። ሰብአዊ ፍጡራን፣ የእግዚአብሔር ወዳጆች፣ ልጆች፣ በፍጥረት ውስጥ አብረውት የሚሠሩ፣እግዚአብሔርን ለማገልገል፣ ግን እርሱን ለማገልገል ብቻ*

*ሳይሆን፣ከሁሉም ይልቅ፣እግዚአብሔርን ለማወቅና እርሱን ለመውደድ የተፈጠሩት።(ዶክተር ስቲቭ ብላክሞር)*

በፍጥረት ሳምንት ስድስተኛ ቀን መጨረሻ፣ ልዩ ግዛቱ እንዲሆን እግዚአብሔር ጽንፈ ዓለሙን ፈጠረና፣ ለእርሱ ክብርን በሚያመጣ መንገድ ምድርን እንዲገዛት ሰውን ሾመው።

ይህን በአዕምሯችን እንያዝና፣ጳውሎስ፣ ወልድ በፍጥረት ውስጥ ስለ ነበረው ሚና ቆላስያስ ምዕራፍ 1፡ ቁጥር 16 የገለጸውን እንመልከት።

*ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሯል፣በሰማያትና በምድር ያሉ፣የሚታዩና የማይታዩ ዙፋናት ቢሆኑ፣ወይም ኃይላት፣ገዦች ቢሆኑ ወይም ባለሥልጣናት፣ሁሉም ነገር በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል(ቆላሰ.1፡ 16)።*

የተባለውን ነገር ከዚህ ምንባብ ልብ በሉ፣ጳውሎስ ዙፋናት፣ሀይላት፣ ገዦችና ባለሥልጣናት ለሚሉት ቃላት አጽንኦት ሰጥቷል። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፍጥረት ስለ ህልውና ብቻ አይደለም። ስለ ፖለቲካዊ ሥልጣንም ነው። ዓለም እውን የሆነችው፣ ልዩ በሆነው በልጁ ሥልጣን ሥር የእግዚአብሔር ልዩ ግዛት ለመሆን ነው።

ተመሳሳይ ግንኙነቶችን ዕብራውያን ምዕራፍ 1 ቁጥር 2 ውስጥ ባሉት በነዚህ ቃላት ውስጥ እንመለከታለን፣

*በዚህ መጨረሻ ዘመን ግን ሁሉን ወራሽ ባደረገውና ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ ለእኛ ተናገረን (ዕብራውያን 1፡ 2)*

የዕብራውያን ጸሐፊ እዚህ ላይ፣ እግዚአብሔር ወልድ "የሁሉም ነገር ወራሽ" ነው በሚለው ሀሳብ መሰረት፣ በመፍጠር ተግባር ሙሉ ሠራተኛ ነበር፣የሚለውን ሀሳብ፣ማለት ፍጥረትን ሁሉ የሚወርስና የሚገዛ ንጉሥ እርሱ ነው ከሚለው ሀሳብ ጋር አያይዞታል። እንደውም ይህ ጭብጥ በምእራፉ በሙሉ ውስጥ ይገኛል።

የፍጥረት ዓላማ እንደ እግዚአብሔር ልዩ መንግሥት ማገልገል መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያለ ማቋረጥ ያስተምራል። አዲስ ኪዳን ደግሞ፣ ይህ መንግሥት፣ ፍጥረት በእርሱ በኩልና በእሱ በተፈጠረበት በእግዚአብሔር ልዩ ልጅ የሚመራ መሆኑን ግልጽ ያደርጋል። እንደውም የወልድ የመፍጠር ስራ የንጉስነቱና የሥልጣኑ መገለጫ ነው ልንልም እንችላለን። እርሱ ስለ ፈጠረው በፍጥረት ላይ ሥልጣን አለው። ስለዚህ፣ ማንኛውም ፍጡር፣በፍቃደኛነትና በታዛዥነት ለእግዚአብሔር ወልድ የመገዛት ግዴታ አለበት።

*እግዚአብሔር ወልድ ጽንፈ ዓለሙን በመፍጠሩ ሥራ የመሳተፉ እውነት፣እንደ ጌታችንና አዳኛችን ከእርሱ ጋር ላለን ግላዊ ግንኙነት በጣም ጠቃሚያችን ነው። ነገር ግን አዳኛችን ያዳነን ከዓለም መንጥቆ እንደማውጣት ባለ መንገድ አይደለም። በዓለም ውስጥ በትክክለኛው መንገድ እንድንኖር በማስቻል ነው እንጂ፤ምክንያቱም ይህ ዓለም እርሱ የፈጠረው ነው። የእርሱ ስለሆነ፣ የእኛም ነው፣እኛ የጌታ ስለሆንን በእግዚአብሔር ፊት በዓለም እንድንኖር በተጠራንበት ሁኔታ ልንኖር የተገባን መሆኑን መረዳት በጣም ጠቃሚያችን ነው። በኢየሱስ የምናውቀው እግዚአብሔር፣የራሱ ያደረገን፣ሀይልና ሥልጣን የእርሱ ነው። በዓለም ባለው መንግሥቱ ውስጥ በአስተዳደሩና በአገዛዙ ውስጥ የመሳተፍ ዕድል የሰጠንም እርሱ ነው። ስለዚህ፣ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት፣እንድንኖር እርሱ በሚፈልገው ሁኔታ በፈጠረው ዓለም ውስጥ እንድንኖር እውቀት፣ ነጻነትና ሥልጣንን ስለ ሚሰጠን በጣም ጠቃሚ ነው።(ዶክተር ጌራልድ በሬይ)*

*ለየት ካሉት የክርስትና እምነት እውነቶች አንዱ፣ጌታችንና አዳኛችን ኢየሱስ ክርሰቶስ ነጻ ማውጣት ብቻ ሳይሆን፣ ጽንፈ ዓለሙን በመፍጠር ውስጥም አስፈላጊ ሚና የነበረው መሆኑ ነው። ጌታችንና አዳኛችን ታዳጊ ወይም ነጻ አውጪ ነው፣ ይህ ብቻ አይደለም፣ በበለጠ ሙላት ፈጣሪና ታዳጊም ነው። ይህ ለእኛ ብዙ አንድምታዎች አሉት። ከነዚህ አንዱ፣የሁሉም ነገር ፈጣሪ የሆነው አዳኛችን ምን ያህል ታላቅ መሆኑን የሚያስታውሰን ነው። በእውነት አስገራሚ አሳብ፣ነው። ወልድ በአንዳች ሁኔታ ከአብ ያነሰ ነው፣ብለን በተሳሳተ አሳብ ሳንመራ፣ በግዙፉ፣ እንዲሁም አስደናቂው ጽንፈ ዓለማችን መፈጠር ውስጥ። ሙሉ ተሳታፊ ስለመሆኑ እርግጠኞች እንድንሆን ያደርገናል። የኢየሱስ ክርስቶስ ልብ ለቤተክርስቲያን ብቻ ሳይሆን፣ ለተፈጥሮ ሥርዓትና ፍጥረት ሁሉ የተከፈተ መሆኑንም ያስታውሰናል ብዬ አስባለሁ። በመጨረሻው ጊዜ ሙሉ በሙሉ ይመጣል ብለን የምንጠብቀው መታደግ፣በመቃተት ላይ ላለው ዓለም መታደግም ይሆናል። በመጨረሻም ይህ፣ ኢየሱስ ክርሰቶስን የሚከተሉ ሁሉ፣ከእርሱ ልብ ጋር የሚመታና፣ እንደፈጣሪዋ ለዚች ዓለምና ለነዋሪዎችዋ የሚጨነቅ ልብ ሊኖራቸው እንደሚገባ የሚስታውስ ነው ብዬ አስባለሁ።(ዶክተር ገሌን ስኮርጂ)*

ከፍጥረት ሳምንት ምልከታ አንጻር ወልድ በፍጥረት ውስጥ የነበረውን የሥራ ድርሻ ከተመለከትን እንግዲህ፣ሰው በኀጢአት የወደቀበትን ሁኔታ ወደ መመልከቱ ለመሄድ ዝግጁ ነን።

## የሰው ውድቀት

የሰው በኀጢአት መውደቅ አሳዛኝ፣ ግን በጣም የታወቀ ታሪክ ነው። በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ውስጥ እንደምንመለከተው፣ እግዚአብሔር የመጀመሪያዎቹን ወላጆቻችንን፣አዳምንና ሔዋንን ውብ በሆነው የኤደን የአትክልት ሥፍራ አኖራቸው። ሥራቸው የአትክልቱን ሥፍራ መጠበቅና በቂ ትውልድ ማፍራት ነበር። ይህ የሆነው፣የሰው ዘር የአትክልቱን ሥፍራ በማስፋትና ምድርን በመሙላት፣ መላው ዓለም ለእግዚአብሔር መኖሪያነት ተስማሚ እንዲሆን ለማድረግ ነበር። ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ውስጥ ግን፣ ሰይጣን በእባብ ተመስሎ በመምጣት፣መልካምና ክፉን ማወቅ የሚያስችለውንና የተከለከለውን ዛፍ ፍሬ እንድትበላ ሄዋንን ፈተናት። ሄዋንም ከበላች በሁዋላ ለአዳም ሰጠችው፣እርሱም በላ። ይህ ነበር የመጀመሪያው የሰው ያለመታመን ወይም አለመታዘዝ ድርጊት። አዳምና ሄዋን የሰይጣንን ምክር አምነው፣የእግዚአብሔርን ስጦታና ትእዛዝ ባለማመን ድርጊቱን ፈጸሙ።

ስለዚህ፣እግዚአብሔር ዘፍጥረት 3 ውስጥ አዳምን፣ሄዋንን እና እባብን በመርገም ለተፈጸመው ኀጢአት አጸፋዊ ምላሽ ሰጠ። በዚህ እርግማን ውስጥ ያሉት ፍርዶች፣የሰውን አለመታዘዝ ውጤቶች በመደምደም፣ እግዚአብሔር ለፍጥረት የነበረውን ዓላማ አዘገዩት። በዚህ ሁሉ ውስጥ የእግዚአብሔር ወልድ ሚና ምን ነበር? የወልድ ሥራ፣ሰዎች ኀጢአት በሠሩ ጊዜ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመተባበር እነሱን መርገም፤በመጨረሻ በመምጣት የሰውን ዘር ከእርግማኖቹ የሚታደግ ተስፋ መሆን ነበር፣ በማለት ለማጠቃለል እንችላለን።

እግዚአብሔር ወልድ ሰው በኀጢአት በወደቀ ጊዜ የነበረውን ሥራ በሦስት መንገዶች እንመረምራለን። መጀመሪያ የውድቀትን ግላዊ ወጤቶች እናጠናለን። ሁለተኛ፣ አጠቃላይ ውጤቶችን እንመለከታለን። ሦስተኛ፣ ከውድቀት በኋላ ለሰው ተሰጥቶት ነበረውን ተስፋ በአጭሩ እንጠቅሳለን። በውድቀት ግላዊ ውጤቶች እንጀምር።

## ግላዊ ውጤቶች

*በሮሜ 5 መሠረት እንግዲህ፣ከሰው በኀጢአት መውደቅ ውጤቶች አንዳንዶቹ በአንድ ሰው፣ስለ አዳም መናገሩ ነው፣ኀጢአት ወደ ዓለም ገባ፣ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ ተላለፈ፣ትርጉሙ ሁሉም ኀጢአት ሠሩ ማለት ሲሆን፣ ሁሉም በእርሱ ኀጢአት ሠሩ ማለት ነው። የሰው ዘርን በሙሉ ወክልዋል። እናም እርሱ ኀጢአት በሠራ ጊዜ፣ኀጢአቱ ለሰው ዘር በሙሉ ተላለፈ። ኀጢአተኛ ባህርይውም ተሸጋገረ። እስቲ አስቡ፣*

*እግዚአብሔር አዳምን በሚፈጥረው ጊዜ፣ አንድ ጠርሙስ መርዝ ውስጡ ጨምሮበት ቢሆን ኑሮ፣ ይህ ትክክል አይደለም፣ግን እንደዚያ አስቡ፣ይህ ቢሆንና፣ እግዚአብሔር አዳምን ፍቃዴን ባትፈጽም ያ ትንሽ ጠርሙስ ይሰበራል ቢለው፣ አዳም የእግዚአብሔርን ፍቃድ ባይፈጽምና ትንሹ ጠርሙስ ተሰብሮ አእምሮውን ቢመርዘው፣በትክክል ማሰብ ባይችል፣ ልቡ ቢመረዝ፣ ትክክለኛ ነገሮችን ባይወድ፣ፍቃዱ ቢመረዝ፣ ትክክኛ ነገሮችን ለመምረጥ ባይችል:: ከዚያም አዳም ልጆች ቢወልድና ኀጢአታዊ ባህርይው ወደ ልጆቹ ቢተላለፍ፣ እንዲሁ የሰው ዘር በሙሉ ከኀጢአተኛ ባህርይና በእግዚአብሔር ላይ ከማመጽ ጋር ቢኖር::(ዶክተር ፈራነክ ባርከር)*

የሰውን በኀጢአት ውስጥ መውደቅ ግላዊ ውጤት የሚገልጡ ብዙ መንገዶች አሉ:: ነገር ግን፣በዚህ ትምህርት ላለን ዓላማ፣ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ከነበረው ህብረት መቋረጥ በመጀመር፣ በአራት ሀሳቦች ላይ እናተኩራለን::

## *የተቋረጠ ህብረት*

*የሰው በኀጢአት መውደቅ በመሠረቱ፣ በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ ነው፤የባህርይው ነጸብራቅ የሆኑ ሞራላዊ ትእዛዛቱን መተላለፍ:: ያ መተላለፍ፣ በማንኛውም ደረጃ ወደ አስከፊ መለየት አመራ:: የመጀመሪውና ከሁሉ የከፋው፣ ከእግዚአብሔር መለየት ነበር:: እንደ ፍጡር፣ በእርሱ አምሳያ የተሠራንና እርሱን ለማክበር የታቀድን እኛ ያን አናደርግም:: በመሆኑም ከእግዚአብሔር ክብር ጎደልን፣ በእርሱ ላይ ስናምጽም፣ እርሱ ይህን ፍጥረት በመርገም፣ በእግዚአብሔርና በፍጥረቱ መካከል መለያየትን አመጣ:: በመሆኑም ሰው ስለ መለየት ያለው ልምድ፣ከዋናው የዋሰትና ምንጫችን፣ ከአስፈላጊነታችን፣ማንነታችን፣ የእግዚአብሔር ፍጡር ከመሆናችንና፣ ከእግዚአብሔር ለይቶናል:: ሰብዓዊ ፍጡራን ሁሉ ደስታችንን፣ማንነታችንን፣በእግዚአብሔር ያለንን እርካታ፣ያን ስናጣ ደግሞ በዓለም ነገር ውስጥ እርካታን የምንፈልግ በመሆናችን እርስ በርሳችን እንከዋን ተለያይተናል:: ሰዎች እንግዲህ፣የርህራሄና የፍቅር መገለጫዎች ከመሆን ይልቅ፣ ለማንነታችን ለምንፈልጋቸው በዚህ ዓለም ነገሮች ውድድር ውስጥ ገብተናል፤በመሆኑም ከሌሎች ሰዎች ጋር ተለያይተናል::(ዶ/ር ኬ.ኤሪክ ቶዊነስ)*

እግዚአብሔር ይህን ዓለም ያቀደው፣ከፍጥረቱ ጋር የሚኖርበት ሥፍራ ለማድረግ ነበር። የአዳምና የሄዋን ኀጢአት ግን፣ ከእግዚአብሔር ለያቸው፣ ከእርሱ ጋር የነበራቸው ሕብረትም ተቋረጠ። አለመታዘዛቸው ሃፍረት ፈጠረባቸው፣በእግዚአብሔር መገኘት ያገኙት የነበረውን እርካታና መተማመንም አጡ። ከእግዚአብሔር ጋር ኤደን ገነት ውስጥ በመራመድና በመነጋገር ፋንታ፣ ከርሱ ተደበቁ። ይህ ሕብረት ከሰው ምልከታ አንጻር መቋረጥ ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔርም መገኘታቸውን ስለ አልፈለገው፣ ከኤደን ገነት አስወጣቸው። በመሆኑም፣ግንኙነቱ እንደገና እንዲመሰረት የሚናፍቀው አንዱ ትልቅ ሰብዓዊ ፈላጎት ተፈጠረ።

በተጨማሪም፣ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት በመቋረጡ ምክንያት በአዳምና በሄዋን መካከል የነበረው የእርስ በእርስ ግንኙነትም ተቋረጠ። ራቁታቸውን በመሆናቸው በማፈራቸውና እርቃናቸውን በበለስ ቅጠል በመሸፈናቸው እውነት ይህ ተረጋግጧል። እግዚአብሔር ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ቁጥር 16 ውስጥ ሰውን በረገመበትና፣ኀጢአት በትዳር ውስጥ የሚፈጠር ችግር ምንጭ መሆኑ በተነገረን ሁኔታ ውስጥም ይህን እንመለከታለን። ስለዚህ፣ሰው እነዚህን ሰብዓዊ ግንኙነቶች ወደ ነበሩበት የሚመልስ መታደግንም ይፈልጋል።

## ጥፋት

ይህን ችግር በተመለከተ ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 5 ቁጥር 18 የሚገልጠውን ተመልከቱ፣

> *በአንድ ሰው መተላለፍ ተነሳ ኩነኔ በሁሉም ሰው ላይ እንደመጣ (ሮሜ 5:18)*

ጳውሎስ፣ የአዳም አንድ አለመታዘዝ በሰው ሁሉ ላይ ፍርድን አመጣ ብሎ አስተማረ። በሌላ አነጋገር፣የአዳምን ኀጢአት፣ የወደቀው ሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ እዳ በማድረግ፣ሁላችንን የመጀመሪያው መተላለፍ ጥፋተኞች እንድንሆን አድርጓል። ይህ የሆነው፣አዳም የሰው ዘር ሁሉ የቃል ኪዳን እራስ ስለሆነ ነው። የወከለው ራሱን ብቻ ሳይሆን፣ሚስቱን እና በተፈጥሮዋዊ የመዋለድ መንገድ ከእነርሱ የሚወለደውን ሰብአዊ ፍጡር ሁሉም ነው። በመሆኑም፣ ከዚህ ጥፋት እና በዚህ ሳቢያ ከሚመጣው ዘላለማዊ ቅጣት ነጻ የሚያደርገን መታደግ እኛም ያስፈልገናል።

ሦስተኛውና የምንጠቅሰው የውድቀት ግላዊ ውጤት መበላሸት ወይም መበከል ነው።

**መበላሸት ወይም መበከል**

መበላሸት ወይም መበከል የሚለው የሥነ መለኮት ቃል የሚያመለክተው፣ የሰብዓዊ ፍጡርን መበከል ነው። የተለያዩ ሥነ መለኮታዊ ባህሎች መበላሸት ወይም መበከል የሚለውን ቃል የሚረዱት በተለያየ መንገድ ነው። ነገር ግን ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ሁሉ የሚስማሙት፣በእግዚአብሔር መወደድን ወይም መመረጥን የሚያሳጣን መሆኑን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሰብዓዊ ፍጡርን መበላሸት ወይም መበከል በተመለከተ ሮሜ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 9-18 ያለውን ጨምሮ ብዙ ቦታ ላይ ይገልጻል።

ለምሳሌ፣ ሮሜ ምዕራፍ 3 ከቁጥር10-12 ያሉትን እነዚህን ቃላት ተመልከቱ፣

> *“ጻድቅ ማንም የለም፣አንድም እንኳ፤አስተዋይ የለም፣እግዚአብሔርንም የሚሻ አንድም የለም። ሁሉም ተሳስተዋል፣በአንድነት የማይጠቅሙ ሆነዋል፣ በጎ የሚያደርግ ማንም የለም፣አንድም እንኳ“(ሮሜ 3፡10-12)*

ስለ ሰው መበላሸት ወይም መበከል የመጽሐፍ ቅዱስን የጸና አስተምህሮ ለማጉላት፣ ጳውሎስ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ከብሉይ ኪዳን የተለያዩ ቁጥሮችን አገናኝቷል።

ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 3 ውስጥ ሲያስተምር፣ ማንም ጻድቅ ቅንና መልካም ነገር በማያደርግበት ሁኔት ጸባያችን የተበላሸ ወይም የተበከለ መሆኑን ገልፆአል። ማንም መረዳት እንዳይችል እውቀታችንም ተበላሽተዋል። ማንም እግዚአብሔርን እንዳይፈልግም፡ ፍቃዳችን ተበክለዋል። ጳውሎስ እንደውም ሰብዓዊ ፍጡር በቅዱሱ አምላካችን ፊት ዋጋ የሌለው ሆንዋል፣ እስከማለት ደርስዋል። በረከቱን ለመቀበል የምንበቃ አይደለንም፤እራሳችንን ነጻ ለማውጣት የምናደርገው ነገርም የለም። ነጻ የሚያወጣን ሰው ያስፈልገናል።

> *ታውቃላችሁ፣20ኛው ክፍለ ዘመን በተጀመረ ጊዜ በዓለም ውስጥ፣ በተለይም በምዕራቡ ዓለም፣ትልቅ ተስፋ የማድረግ ሁኔታ ነበር። ይህ የሆነበት ምክንያት፣በሳይንስ ማደግ፣ትምህርት በሰፊው በመኖሩ፣በግኝቶች-ቴክኖሎጂያዊ ዕድገት..ወዘተ፣በፈላስፋዎች፣ ማህበራዊ ሳይንቲስቶች እና በሊበራል ሥነ መለኮታውያን ዘንድ የባለተስፋነት ትልቅ አባዜ ነበር፣ሃያኛው ክፍለ ዘመን ጦርነት የማይኖርበት የሰላም ክፍለ ዘመን ይሆናል የሚል። ሀያኛው ክፍለ ዘመን ሰብዓዊ አመክንዮ የሚገዛበት ክፍለ ዘመን ይሆናል፣በመሆኑም ምክንያታውያን ወይም አመዛዛኝ ፍጡሮች እርስ በርሳቸው አይጋደሉም። ስለዚህ፣ወደዚህ ብዙ ነገር ወደ ሚጠበቅበትና ሰላም ወደ ሚሰፍንበት ክፍለ ዘመን በመዳረስ ላይ ነበርን። አያችሁ፣እንዲህ ባለው ነገርና በኮሙኒዝም ውስጥ የነበረው ችግር፣በማህበራዊ ህልውና መፈራረስ ያበቃውና ተስፋ የተደረገበት ስነ*

*ሕዝቡ ነበር። ይህ የሆነበት ምክንያት፣የኀጢአት አስተምሮ የሌለው መሆኑ ነው። ታዲያ ምን ሆነ? የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ተከሰተ። የቦልሾቪክ፣ማለት ኮሙኒስቶች አብዮት ነበር። ከዚያም ትልቅ እልቂት የሆነበት ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተከተለ፣ ሂተለርን ታውቁታላችሁ፣ናዚዝምን...ወዘተ። እና በዚህ ምክንያት፣ለማጠቃለል፣በሃኛው ክፍለ ዘመን 112.8 ሚሊዮን ያህል ሰዎች በጦርነት ተገድለዋል። ስለጦርነት ብቻ ነው የምናገረው። የተመዘገበ መረጃ ቁጥሩን እንድናሰላ በፈቀደልን መሠረት ይህ ሲቪሎችንና ወታደሮችን የካትታል። ይህ ቁጥር፣ከዚያ በፊት በነበሩት አራት ክፍለ ዘመናት የደርሱት ጉዳቶች ተደምረው በአራት እጥፍ ይበልጣቸዋል። ይህ ምን ይነግረናል? አንድ የተሳሳተ ነገር መኖሩን። ማህበራዊ ሁኔታዎች ብቻ ሳይሆኑ፣እውቀት ሁሉ፣ ሳይንሳዊ እድገትና የስልጣኔ በረከቶች ሁሉ... ሰብዓዊ ተፈጥሮን በተመለከተ አንድ መሰረታዊ ስህተት አለ። ይህም እኛ ክርስቲያኖች "ኀጢአት" የምንለው ነገር ነው። ይህ ቃል በመገናኛ ብዙሃንና በከፍተኛ ትምህርት አካባቢ...ወዘተ፣ ተወዳጅ አይደለም። ሬይን ኒቡክር የተባለው ጸሐፊ እንደሚለው ግን፣" የኀጢአት ክርስቲያናዊ አስተምህሮ፣ከአስተምህሮዎች ሁሉ ትንሹ ነው፤ነገር ግን በየቦታው ብዙ ተጨባጭ ማስረጃ እናገኝበታለን"...(ዶክተር ፔተር ኩዝሚክ)*

የውድቀት አራተኛው ውጤት፣ሰብዓዊ ፍጡር በመከራ፣በበሽታና በሞት ውስጥ ማለፍ መጀመሩ ነው።

### *መከራ፣በሽታና ሞት* -

ሰው በኀጢኣት ከመውደቁ በፊት፣ ህይወት ፍጹምና የተሳካች ነበረች። ሰብዓዊ ፍጡራን ስቃይ፣ወይም ችግር፣ወይም በሽታ፣ መይም ሞት አልነበረባቸውም። አዳምና ሔዋን ኀጢአት ከፈጸሙ በኋላ ግን፣እግዚአብሔር እነሱንና ዘራቸውን ሁሉ ረገመ።

*በኀጢአት ውድቀት ምክንያት እግዚአብሔር በሰዎች፣እንዲሁም በተፈጥሮ ሁሉ ላይ ፈረደ። ለምሳሌ ፣አዳምና ሄዋን ከውድቀት በፊት ያከናውኑት የነበረ ሥራ፣ በመጣር ወይም በመልፋት የሚከናወን ሆነ፤ከዚህም የተነሣ ሰዎች ከሥራ ጋር ያላቸው ግንኙነት የመውደድና የመጥላት ጉዳይ ሆነ። በወንዱና በሴቲቱ መካከል ያለው ግንኙነትም ተበላሸ፣ ተዛባም። ብዙ የእግዚአብሔር አምሳያዎችን ለማብዛት የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነው ልጅ መውለድ፣ስቃይ የሞላበት ሆነ። እና መሰረታዊው፣አጠቃላይ ውጤት፣እንዲደሰቱበት እግዚአብሔር ለአዳምና ሄዋን የሰጣቸው ነገር በመደሰቻነቱ ቢቀጥልም፣በአንዳንድ ሁኔታዎች*

*ስለሳቱና ስለተዛቡ ሙሉ በሙሉ ደስተኞች አልነበሩም። (ዶክተር ሳይመን ቪበርት)*

እግዚአብሔር በሰብዓዊ ፍጡራን ላይ የጣለውና ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ከቁጥር 16-19 ውስጥ ያለው ፍርድ እንደሚከተለው ይነበባል፣

ሴቲቱንም እንዲህ አላት፣"በምጥ ጊዜ ጭንቀሽን አበዛለሁ፣በስቃይም ትወልጃለሽ፣ ፍላጎትሽም ወደባልሽ ይሆናል፣እርሱም የበላይሽ ይሆናል" አዳምን እንዲህ አለው፣"የሚስትህን ቃል ሰምተህ ከእርሱ አትብላ ብዬ ያዘዝሁህን ዛፍ በልተሃልና፣ከአንተ የተነሣ ምድር የተረገመች ትሁን፣ በህይወትህ ዘመን ሁሉ ምግብህን ጥረህ ግረህ ከእርስዋ ታገኛለህ፣ምድርም እሾህና አሜኬላ ታበቅልብሀለች፣ ከቡቃያዋም ትበላለህ፣ ከምድር ስለተገኘህ ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ እንጀራህን በፊትህ ላብ ትበላለህ፣ ዐፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ"(ዘፍጥረት 3፡ 16-19)።

እነዚህ እርግማኖች በሰብዓዊ ፍጡራን ላይ ስቃይና መከራን ማምጣት በቻ ሳይሆን፣እንዲፈጽሙት እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሥራም እንዳያከናውኑ ከልክለዋቸዋል። ሰብዓዊ ፍጡራን፣ በመባዛትና ምድርን በመሙላት፣ በምድር ላይ በመሥራትና በመጠበቅ፣ እንዲሁም ምድርን በመግዛትና የእግዚአብሔርን መንግሥት በማስፋፋት ሥራቸው ችግር ይገጥማቸው ጀመር።

ከዚያም በከፋ ሁኔታ ሰው ይሞት ጀመር። እናም እነዚህ እርግማኖች ለሰው ዘር ሁሉ ተላለፉ። በመሆኑም፣ እግዚአብሔር ለሰብዓዊ ፍጡራን ያለውን ዓላማ ለማከናወን ከፈለግን፣ ከነዚህ መከልከሎች ነጻ የሚያወጣንና ወደ ተባረከ እንዲሁም ወደ ደስተኛ ኑሮ የሚመልሰን ታዳጊ ወይም ነጻ አውጪ ያስፈልገናል።

*የሰብዓዊ ፈጡር ውድቀት ውጤቶች፣የሰው ዘር በራሱ መንገድ መጉዋዙ ነው። ሀጢአት ለእግዚአብሔር ትእዛዛት አለመገዛት ሲሆን፣ሰብዓዊ ፍጡራን ደግሞ ፍጹማን አይደሉም። ከእንግዲህ ወደ እግዚአብሔር መሥፈርት ሊደርሱ አይችሉም። በዚህ ሁኔታ ነው ከውድቀት በሁዋላ ከእግዚአብሔር የተለየነው እና፣ የሰው ዘር ሁሉ ከሞት እውነታ ጋር የተጋፈጠው። ያለ ልዩነት፣ ማንም በእግዚአብሔር ዐይን ጻድቅ አይደለም። ምንም እንኩዋን ሰብዓዊ ፈጡራን አሁንም የእግዚአብሔር አምሳያ ቢሆኑ፣የተበከሉ ወይም የተበላሹ ናቸው። በክርስቶስ ነጻ ሳይወጣ፣ማንም በተፈጥሮው ወደ እግዚአብሔር አይቀርብም። በእግዚአብሔር መልካምነት ደረጃም ለመኖር አንችልም። (ዶክተር ስቴፈን ቻን)*

*በዚህ ምክንያት ሰዎች ታዳጊ ወይም ነጻ አውጪ ስለሚሹ እግዚአብሔር ራሱ ነጻ አውጫጣቸው እንዲሆን ይፈልጋሉ። የኀጢአት ባህርይ የእግዚአብሔር ተጻራሪ ነው። እግዚአብሔር ጽንፈ ዓለሙን ወደ ህልውና ያመጣ አካላዊ ያልሆነ ኃይል አይደለም። እግዚአብሔር አካል ነው፣በሥላሴ ትምህርት፣ እግዚአብሔር አብ፣ወልድ፣መንፈስ ቅዱስ። እግዚአብሔር በህልውናው ጥልቅ በሆነ ሁኔታ አካል ነው፣በመሆኑም ኀጢአታችን በእግዚአብሔር ላይ በግል የሚፈጸም በደል ይሆናል። ኀጢአታችን፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሊነግረን ከሚሞክረው ነገር እንደምረዳው፣ ከምንም ነገር ይበልጥ ፈጣሪያችንን መካድ ነው። ስለሆነም፣ይህን ለማስተካከል ልናደርግ የምንችለው ነገር የለም። ክህደት፣ የተካደው ወገን ብቻ አንዳች ነገር ሊያደርግበት የሚቻለው ጉዳይ ነው። በመሆኑም፣እግዚአብሔር ከታደገንና፣የተቋዋረጠ ግንኙነታችንን ካደሰው ብቻ ነው ነጻ ልንወጣ የምንችለው። ኀጢአት በሰው ሁኔታ ላይ ካደረሰው ነገር የተነሳ ታዳጊ ያስፈልገናል። ኀጢአት በወጥመድ ይዞናል። ከእግዚአብሔር በራቅንና በራሳችን በታመንን ጊዜ፣ ስበት በሚመስል ወጥመድ ይዞናል። የእግዚአብሔር ቸርነት እንድናመልጥ ካልፈቀደልንና ልባችን፣ አንዲሁም ህይወታችን ወደ እግዚአብሔር ካልተመለሰ፣ ከራሳችን ኀጢአቶች ልናመልጥ አንችልም። ስለዚህ፣ መጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነገሮችን ትክክል ለማድረግ የሚችል ታዳጊ ወይም ነጻ አውጪ፣ እንዲሁም ወደ ኀጢአተኛው ሁኔታችን የሚመጣና የኀጢአትን ኃይል የሚሽር ታዳጊ ብቻ ነው ሊድነን የሚችል።(ዶ/ር ስቲብ ብላክሞር)*

የሰብዓዊ ፍጡርን በኀጢአት መውደቅ ተከትሎ የመጣውን ግላዊ ውጤት ከተመለከትን እንግዲህ፣ ጽንፈ ዓለማዊ ውጤቱን ለማየት ዝግጁ ነን።

## ጽንፈ ዓለማዊ ውጤቶች

አመጻችን በጽንፈ ዓለሙ በሙሉ መርገምን አመጣ እንጂ፣ ሰው በእግዚአብሔር መንግሥት ዓላማ ውስጥ በጣም ማዕከላዊ ነበር። ከዚያን ጊዜ ወዲህ፣ ሰው ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ፣ ለራሱ ክብር መኖርን ቀጠለ። አንዳችን በሌላችን ላይ ያልተገባ ነገርና ግፍ ፈጸምን። በእግዚአብሔር ፍቃድ ላይ ያለ ማቋረጥ አመጽን። በመሆኑም፣ መንግሥቱ በምድር ላይ እንዳትሰለጥን እርሱም እንደ መልካም ንጉሥና ፈጣሪ ፍጹም ክብሩ እንዳይገለጥ ሆነ። ተፈጥሮአዊው ዓለምም በዚህ ምክንያት ተጎድቷል። መበስበስና ሞት ምድርንና በላይዋ ያሉ ፍጥረታትን ሁሉ በከሉ፣አቃለሉዋቸው። ፍጥረት በማንኛውም መልኩ ድነትና መታደግን ይፈልጋል።

በዚህ ትምህርት ውስጥ፣የእግዚአብሔርን መንግሥት ከማዘግየቱ እውነት በመጀመር፣በሁለት ጽንፈ ዓለማዊ የውድቀት ውጤቶች ላይ እናተኩራለን።

*የእግዚአብሔር መንግሥት መዘግየት*

በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ቁጥር 8 ውስጥ እደምናነበው፣ እግዚአብሔር ዓለምን በፈጠረ ጊዜ፣ ገነት የነበረው ክፍል፣የኤደን የአትክልት ሥፍራ ብቻ ነበር። ሌላው የዓለም ክፍል ያልለማና ምድረ በዳ ነበር። ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 28 ውስጥ እንደተጻፈው. ምድርን መግዛት፣ መላው ዓለም የእግዚአብሔርን የአትክልት ሥፍራ እንዲመስል ማልማትና በሁሉም ሥፍራ ሰብዓዊ ማህበረሰብ መመሥረት የሰው ሥራ ነበር። በክብር የተሞላው ሰማያዊ አገዛዙ በምድራዊው ፍጥረቱ ላይ በሚገባ መስፋፋቱን ለማረጋገጥ፣እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ ነገሥታት ምድርን እንድንገዛትም ታስበን ነበር። ይህ ሥራ ሲጠናቀቅ፣ እንደ ምድራዊ ልዩ መንግሥት በዓለም ላይ ለመኖር የእግዚአብሔር አቅድ ነበር።

ነገር ግን፣የሰው ኀጢአት ውስጥ መውደቅ፣የዓለምን በተገቢው ሁኔታ መልማትና፣የእኛን ገዥዎችዋ መሆን አዘገየው። የእግዚአብሔርን መንግሥት መምጣትም አዘገየ። ምድርን ለማልማትና ለመግዛት ያደረግነው ሙከራ በኀጢአት የተበላሸ ነበር። በመሆኑም፣እኛ ያዘጋጀነው ዓለም ለእግዚአብሔር መኖሪያነት ተስማሚ አልሆነም። ያለ ምንም ጥርጥር ሰብዓዊ ፍጡራን በአጥጋቢ ሁኔታ ምድርን ሞልተዋታል። ነገር ግን፣ የገነባናቸው ማህበረሰቦች፣እንድንሰራው ከታዘዝነው ፍጹም ዓለም በጣም የራቁ ናቸው። ጦርነቶች፣ወንጀል፣ጸብ፣ጥላቻና ሀሰተኛ ሀይማኖት ተስፋፍተዋል፤እናም ቤተክርስቲያን ውስጥ እንኳን ብዙ ጊዜ እምነትና ለእግዚአብሔር መሰጠት የሚጎድላቸው ሰዎች እናገኛለን። በዓለም ውስጥ ባለው በዚህ ሁሉ ኀ ጢአት ምክንያት፣የእግዚአብሔር መንግሥት ገና በሙላት አልመጣችም።

ጴጥሮስ በ2ኛጴጥሮስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 11 እና 12 ውስጥ ስለዚህ ችግር ሲገልጥ እንዲህ ብሏል፣

> *በቅድስናና በእውነተኛ መንፈሳዊነት ልትኖሩ ይገባችኋል፣ደግሞም የእግዚአብሔርን ቀን እየጠበቃችሁ መምጫውን ልታፋጥኑ ይገባል (2ጴጥ 3፡11-12)።*

በአንድ ሁኔታ፣ እግዚአብሔር በፈለገ ጊዜ ዓለምን ከኀጢአት ሊያጸዳ ስለሚችል፣ ደስ ባለው ጊዜ መንግሥቱን ወደ ምድር ሊያመጣ ይችላል። የእግዚአብሔር እቅድ ግን፣ይህን በታዳጊው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ማድረግ ነው። በዚህ ምንባብ ጳውሎስ ያስተማረው፣በዓለም ውስጥ ያለውን ክፉ ነገር በመዋጋት፣ፍጥረትን ወደ መጀመሪያ ግቡ እንዲሄድ ማድረግን ልንጀምርና

እግዚአብሔር በምድር ለመኖር የሚመጣበትን ቀን ልናፈጥን እንችላለን በማለት ነው።

ሌላውና በሁለተኛነት የምንጠቅሰው የጽንፈ ዓለማዊ ውድቀት ውጤት፣ ፍጥረት ሁሉ አሁን የከንቱነት ተጠቂ መሆኑን ነው።

### *ለከንቱነት መገዛት*

በሽታና መከራ በሰዎች አኗኗር ውስጥ በገባ ጊዜ፣የሌላው ፍጥረት ሰላምና ምርታማነትም ታወከ። ምድርም ስለተረገመች እሾህና አሜከላ ማብቀል ጀመረች፣እናም ፍጥረት በሙሉ በሥርዓት ማጣትና በመበከል ተቸገረ።

ሮሜ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 20-22 ባለው ክፍል፣ጳውሎስ ይህን እርግማን፣ሲገልጽ፣ ፍጥረት ተስፋ መቁረጥ ተጭኖታል፣በመበስበስ ባርነት ተይዟል፣እንደምትወልድ ሴት በምጥ ያቃስታል፣ ብሏል። በሌላ አነጋገር፣ፍጥረት የታለሙለትን መልካም ነገሮች አያፈራም፣ እግዚአብሔር እንደ አቀደው ፍጹም የሆነ ዓለም ለመሆን እንኳን አይችልም።

በዙሪያችን ያለውን ዓለም ላንድ አፍታ መመልከቱ፣ይህ ምን ያህል እውነት መሆኑን ያረጋግጥልናል። አውሎ ንፋሶች ጠረፎቻችንን ያወድማሉ። የመሬት መንቀጥቀጦች መንደሮችንና ከተሞችን እንዳልነበሩ ያደርጋሉ። አንዳንዴ ጎርፎች መንደሮችን ይጠራርጋሉ። ነፍሳት፣ እንስሳት እና በሽታ አዝርእትን ያወድማሉ። በሽታና አደጋ በሚሊዮን በሚቆጠሩ ሰዎች ላይ መከራና ሞት ያስከትላሉ። የውድቀት ወጤቶች የትም አሉ። ዓለም ትክክለኛ የምትሆንበት ብቸኛ መንገድ፣እግዚአብሔር ፍጥረትን ከዚህ መርገም መታደጉ ነው።

> *አዳምና ሄዋን ኃጢአት መሥራታቸው በፍጥረትና በሰው ላይ ያስከተለው ወጤት፣ ሰው ከተፈጠረለት ዓላማ አንጻር ሲታይ፣እጅግ ግዙፍ ነው። በዘፍጥረት የተነገረን፣ሰው ወንድና ሴት ሆኖ የተፈጠረው፣ምድርን እንዲገዛት ነበር። በእግዚአብሔርና በተፈጥሮ መካከል አገናኝ የሆነው ሰው ያደረገው ነገር ተፈጥሮን ሁሉ አወሳስቦታል። አዳም ከአፈር በተፈጠረበት መንገድ ይህ ሲታይ፣ የፍጥረት እድል ሰዎች ከሚፈጽሙት ድርጊት ጋር የተሳሰረ ነው። አዳምና ሄዋን ኃጢአት በሰሩ ጊዜ አረም አየን፣ስለዚህ አሁን ዓለም ለህይወትና ለፈጥረት ጠላት ነው። በመሆኑም ተፈጥሮን፣ወደ እግዚአብሔር ሥርዓትና ከእርሱ ጋር ወደሚደረግ ግንኙነት ወደ ፊት በመግፋት ወይም በመምራት ፋንታ በተቃራኒው ፍጥረትን በሰው ሕግ፣በሰው የተሳሳተ ሕግ ወደ ጥፋት እየመራ ከእግዚአብሔር በማራቅ ላይ ነው.... ጳውሎስ ወደዚህ ሃሳብ በመመለስ ሮሜ 8 ውስጥ በዓለም*

*ውስጥ በመከናወን ላይ መከራ፣ተፈጥሮዋዊ ጥፋቶች፣ የምንታመምበት በሽታ፣ሊሆን ይችላል፣እነዚህ ሁሉ ለከንቱነት ከተዳረገው ፍጥረት ጋር የተያያዙ ናቸው:: በእጃችችን ውስጥ በመሆናቸውም፣በአጠቃላዩ ኀጢአታዊ አሰራር ሥር ጠፍተዋል:: ጳውሎስ ግን ለፍጥረት ሰውኛ ባህርይ በመስጠት እንዲህ ብሏል፣"ፍጥረት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ በጉጉት ይጠብቃል" ምክንያቱም፣ፍጥረት ሰው ካደረገው ነገር የተነሣ እንደጠፋ፣በእግዚአብሔር ሥር በተገቢው ሁኔታ በሚሠሩ ሰብዓዊ ፍጡራን በኩል ነው የሚድነው፣ገና ባናየውም:: ግን እናያለን፣ሁለተኛው አዳም ክርስቶስ ሲመለስና ሰው እንዲያደርገው የተፈጠረበትን ስራ ሲረከብ፣ፍጥረት በእግዚአብሔር አመራር ሥር መሆን ይገባው በነበረ መንገድ እንዲሰራና በዚያ ሁኔታ አገዛዙ እንዲከናወን ፍጥረትን በሚያዝበት ጊዜ ይህን እናያለን:: ኢሳይያስ 11 ውስጥ በተነገረው ትንቢት መሰረት በእንስሳት ዓለም፣እንዲሁም በሰዎችና በእንስሳት መካከል ሰላም በሚመሥርትበት ጊዜ ይህን አናያለን:: በመሆኑም ነገሮች እንዲሆኑ በታቀደው መሠረት የፍጥረትን የከበረ ሥርዓት መያዝ በጉጉት በመጠበቅ ላይ ነን:: ሰው ምስሉን ተሸካሚ እንዲሆን እግዚአብሔር ያለውን ፍቃድ ለፍጥረት በማምጣት የአስታራቂነት ሚና ያለው ሰብዓዊ ፍጡር ነው::(ዶክተር ጆን ማኪንሌይ)*

ሰው በኀጢአት በመውደቁ ምክንያት የመጡትን ግላዊ እና ጽንፈ ዓለማዊ ውጤቶች ከተመለከትን እንግዲህ፣ከውድቀት በሁዋላ ወልድ የሚሰጠንን ተስፋ ለመመልከት ዝግጁ ነን::

**ተስፋ ለሰብዓዊ ፍጡር**

እግዚአብሔር ሰውን ለመታደግ ያለውን ዕቅድ ለመግለጥ ረጅም ጊዜ አልወሰደም:: እንደውም ለሰው ዘር የመጀመሪያው የተስፋ ብልጭታ የመጣው፣በረገማቸው ጊዜ ነው:: ዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ቁጥር 17 ውስጥ እንደተገለጸው ሰው መልካሙንና ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ ፍሬ ከበላ እንደሚሞት አስጠንቅቆት ነበር:: አዳምና ሄዋን ከተከለከለው ፍሬ በበሉ ጊዜ ግን፣ወዲያው አልሞቱም:: ከዚያ ይልቅ፣ እግዚአብሔር ሞታቸውን በማዘግየት፣ምህረቱን አሳየ:: እንደውም ሰው እንዲያገለግለው በመፍቀድ ምህረቱን ይበልጥ ገለጠ:: ለፍጥረት ካለው እቅዱ ውስጥ ከማውጣት ይልቅ፣ሰዎቹን በፍጥረት ማዕከላዊ ሥፍራ እንዲቆዩ አደረገ::

እግዚአብሔር ከዚያም የበለጠ አንድ የምህረት ሥራ አደረገ፡ የዲያብሎስን እቅድ ሰብሮ ሰዎችን ወደ ታማኝነት የሚመልስ ታዳጊ እንደሚልክ ተስፋ ሰጠ:: የዚህ ታዳጊ መገለጫ ብዙ ጊዜ፣"የመጀመሪያው ወንጌል" በመባል

የሚጠቀስ ሲሆን፣አዳምና ሄዋን ሃጢአት ከሰሩ በኂላ እግዚአብሔር እባብን በረገመበት ክፍል ውስጥ ይገኛል፣

ይህን እርግማን ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ቁጥር 15 ውስጥ ተመልከቱ፣

> *"በአንተና በሴቲቱ በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነጥን አደርጋለሁ፣ እርሱ እራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተ ተረከዙን ትቀጠቅጣለህ" (ዘፍጥረት 3፡15)*

በውድቀት ውስጥ አዳምና ሄዋን ከእግዚአብሔር ይልቅ ከአመጸኛው እባብ ጋር ወገኑ። ያኤም እንኳን እግዚአብሔር ሕዝቡን አልተወም። እባብን በረገመበት ቃል ውሰጥ፣ በመጨረሽ የሴቲቱ ዘር እባቡን በማሸነፍ ሰብዓዊ ፍጡርን እንደሚያድን እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቷል።

ራዕይ ምዕራፍ 12 ቁጥር 9 እና ምዕራፍ 20 ቁጥር 2 እባቡ ዲያብሎስ መሆኑን ያስተምራል። ይህ የመጀመሪያ ወንጌል፣በተራ እንስሳ ላይ ከሚወሰድ የተገቢ ቅጣት ተስፋ የበለጠ መሆኑን ወንጌላውያን የሥነ መለኮት ሰዎች በማያወላዳ ሁኔታ ተረድተውታል። የእባቡን እራስ የሚቀጠቅጥ ታዳጊ ለመላክ እግዚአብሔር የሰጠው ተሰፋ፣ ሰዎችን ከኀጢአታቸው ውጤት ለማዳን የተሰጠ ተስፋ ነበር፣ሰዎችን ለዲያብሎስ ካላቸው ተዛማኝነት ለመመለስ እና እንደ ታማኝ የመንግሥቱ ዜጎች ከእርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመመለስ። እነዚህ የመጀመሪያ የወንጌል ምስሎች እግዚአብሔር እርቃንና ሃፍረታቸውን ለመሸፈን አዳምና ሄዋንን የቆዳ ልብስ ባለበሰበት ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ቁጥር 21 ውስጥ ቀጥልዋል። ይህ እግዚአብሔር ለሰዎች ያለውን የማያቋርጥ ፍቅርና ቸርነት መግለጥ ብቻ ሳይሆን፣የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚታደግና ኀጢአታቸውን የሚሸፍን ሙሉ መስዋዕት የሚቀርብበትን ቀንም የሚተነብይ ነው። አዲስ ኪዳን ግልጽ እንደሚያደርገውም፣ይህ መስዋዕት እራሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል።

በዘለዓለም እና በፍጥረት ውስጥ የወልድን ሥራ ከተመለከትን እንግዲህ፣ወደ ዋነኛውና ሦስተኛው ጉዳይ ማለትም፣ወልድ በመታደግ ውስጥ ወደ ፈፀመው የመዋጀት ሥራ ለመሸጋገር ዝግጁ እንሆናለን።

## 4 መዋጀት

የአዳምና የሄዋን በኀጢአት መውደቅ በሰብዓዊ ፍጡርና በሌላው ፍጥረት ላይ አስከፊ ውጤት ነበረው። እግዚአብሔር ግን ከኀጢአታችን እንኳን በላይ ነው። የመጀመሪያዎቹ ወለጆች የሰውን ዘር ከጣሉት በሁዋላ ወዲያው እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የማዳን እቅድ ገለጸ። ከመጀመሪያው ነው እግዚአብሔር፣

ለኀጢአተኞች ድነትን የሚያመጣውንና መላውን ፍጥረተ ዓለም ወደ ነበረበት የሚመልሰውን ልጁን ቤዛ ወይም ታዳጊ አድርጎ የሾመው።

የመዋጀት ታሪካዊ ጊዜ፣ ከዘፍጥረት 3 ውድቀት በሁዋላ ወዲያው እንደ ጀመረና፣ ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ እስከ ሚከናወነው የሰማይና ምድር ማለፍ ድረስ የሚቀጥል አጠቃላይ ዘመን እንደሆነ አድርገን ተገንዝበናል። በዚህ የመዋጀት ጊዜ የወልድ ሥራ፣ በተለይ ለኀጢአተኞች በሚደረግ የመዋጀትና የድነት ጊዜነት ይታወቃል። ወልድ ኀጢአተኞችን ማዳን የጀመረው፣ወዲያው ከውድቀት በሁዋላ፣ ከሄዋን ልጆች አንዱ ወደፊት በሚያመጣው መዋጀት ላይ ተመሥርቶ አዳምና ሄዋን ከእግዚአብሔር ምህረትን ባገኙ ጊዜ ነው። እናም በዘመናት ሁሉ ኀጢአተኞችን ማዳኑን ቀጠለ፣ኀጢአታቸውን እየተናዘዙ ወደ እርሱ የሚመለሱትን ሁሉ።

ሦስት ዋና ዋና ሃሳቦችን በመመርመር፣ በመዋጀት ጊዜ የነበረውን የወልድን ሥራ እንመለከታለን። አንደኛ፣የወልድን ኀጢአተኞችን የመዋጀት ዓላማ፣ሁለተኛ፣ለኀጢአተኞች ድነትን እንደሚሰጥ አብ ለወልድ የገባለት ቃል፣ሦስተኛ፣ይህን መዋጀት ለማከናወን ወለድ የፈጸመው ሥራ። ሀጢአተኞችን በመዋጀት የወልድ ዓላማ ምን እንደሆነ እንመልከት።

**ዓላማ ወይም ምክንያት**

ኀጢአተኞችን በመዋጀት ረገድ የወልድ ዓላማ ውስብስብ ስለሆነ፣ለመግለጥ የሚቻለው በተለያየ መንገድ ነው። ለሥላሴ ክብርን ለማምጣት ባለው ፍላጎት ተነሣሣ። ተፈጥሮ የተሠራበትን ዓላማ እንዲያከናውን ለማድረግ ባለው ፍላጎት ተነሣሣ። ለጽድቅና ምህረት በነበረው ፍላጎት ተነሣሣ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ፣ ወልድ በመዋጀት ሥራ ውስጥ ያለውን ፍላጎት ወይም ዓላማ ለመግለጫነት ከሚጠቀምባቸው በጣም የታወቁ ቃላት አንዱ፣“ፍቅር“ የሚለው ነው፣ፍቅር ለእግዚአብሔር፣ፍቅር ለፍጥረትና ፍቅር ለሰብዓዊ ፍጡር። ይህ ፍቅር ደግሞ በወልድ የተወሰነ ሳይሆን፣ሦስቱም የሥላሴ አካላት የተካፈሉት ነው።

> *እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ፣ሊያድነን ፈለገ። መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ ግልጽ ነው። “እግዚአብሔር ፍቅር ነው“ ዮሐንስ 3፡16 አንዱና በዓለም በጣም የታወቀ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በመሆን ይታወቃል፣“እግዚአብሔር ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና...“ እንዲያድንና እንዲዋጅ ምንድነው ያነሣሣው? ፍቅሩ ነው። ለፍጥረቱ፣በተለይም ለሰብአዊ ፍጡር ያለው እቅድ፣ ከእርሱ ጋር በህብረት እንዲኖር፣ በእርሱ እንዲከናወን፣ በዚያውም ሰዎች እርሱን የሚያወቁበትን መድረክ ለመክፈትና በአጠቃላይ እንደ መልካምና አፍቃሪ አምላክነቱ እንዲከብር*

*ነው:: ስለዚህ፣ እግዚአብሔር እንዲዋጀን የሚያነሣሣው ለእኛ ያለው ፍቅር ነው::(ዶር ስቲቭ ብላክሞር)*

በሥለሴ ሦሥት አካላት መካከል ባለው ፍቅር በመጀመር፣ወልድ በመዋጀት ውስጥ ከነበረው ሥራ ጀርባ የነበረውን የእግዚአብሔር አነሣሽ ፍቅር እንመረምራለን::

## ሥላሴ

እግዚአብሔር ሰብዓዊ ፍጡራንን ለመዋጀት የመረጠው፣ ወዶን ስለ መሆኑ የሚያጠራጥር ነገር የለም:: ይሁን እንጂ፣ከምንረሳቸው ዝርዝር ነገሮች አንዱ፣እግዚአብሔር ለሰው ያለው የመዋጀት ፍቅር፣አብ ለወልድ ያለው ፍቅር ገጽታ መሆኑን ነው::

ጳውሎስ ኤፌሶን ምዕራፍ 1 ከቁጥር 4-6 ባለው ክፍል፣አብ ሊያድነን የወሰነበትን ሁኔታ የገለጠበትን መንገድ ተመልከቱ፣

> *በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በእርሱ መርጦናልና:: በፍቅር፣በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቹ እንሆን ዘንድ እንደበጎ ፈቃዱ አስቀድሞ ውነን፣ይኸውም በሚወደው በእርሱ በኩል በነጻ የተሰጠን ክቡር የሆነው ጸጋው እንዲመሰገን ነው::(ኤፌሶን 1:4-6)*

እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ፣በወደደው ልጁ በኩል ሊዋጀን መውደዱን ጳውሎስ በዚህ አጭር ምንባብ ሶስት ጊዜ ጠቅሷል:: ከነዚህ ነጥቦች አንዱ፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር፣ አብ ለልጁ ያለው ፍቅር ውጤት ነው:: በሥላሴ መካከል ያለው ፍቅር ነው የመዋጀታችን የመጨረሻ ዓላማ:: ሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 39 እና ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 14 ውስጥም ተመሳሳይ ትምህርት እናገኛለን::

አብ ለወልድ ያለው ፍቅር ለመዋጀታችን ወሳኝ የመሆኑን እውነት አዲስ ኪዳን ደጋግሞ ያስታውሳል:: በኢየሱስ መጠመቅና፣ ማቴዎስ ምዕራፍ 3 ቁትር 17፣ ምዕራፍ 17 ቁጥር 5፣ እንዲሁም 2 ጴጥሮስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 17 ውስጥ በተገለጠው መለወጥ ጊዜ አብ ይህን አረጋግጧል:: ኢየሱስ ዮሐንስ ምዕራፍ 3 ቁትር35 እና ምዕራፍ 5 ከቁጥር 20 እስከ 23 ባለው ክፍል ለመዋጀትና ለመፍረድ ያለውን ሥልጣን በገለጠ ጊዜ ይህን ጠቅሷል:: ጳውሎስም ቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 13 እና 14 ውስጥ መዋጀት፣ አብ የወደደው ልጁ መንግሥት ዜጋ መሆን መሆኑን ገልፆአል::

ይህ ፍቅር አቅጣጫ አልባ አይደለም። ሥላሴን ለማክበርና ለመታዘዝ መፈለግን ይጨምራል ማለትም የእግዚአብሔር ክብር እንዲጎላና እንዲገለጥ፣አላማው እንዲከናወን፣በፍጥረት ሁሉ ላይ ንጉሥ መሆኑ እንዲታወቅና እንዲመሰገን ማለት ነው።

> *እግዚአብሔር የሚዋጀን፣ ያለ እኛ ለመኖር ስለ ማይችል፣የተዋጁ ሰብዓዊ ፍጡራን ከሌሉ ሊኖር ስለ ማይችልና፣ ብቸኛነት ስለ ሚሰማው አለመሆኑን መገንዘቡ ይጠቅማል። እግዚአብሔር በራሱ ሙሉ ነው። ያልተሟላ ፍላጎት የለውም። እኛንም ሆነ ሌሎች ፍጡራንን ለምንም ጉዳይ አይፈልገንም። ስለዚህ እግዚአብሔር የሚፈጥረው፣ የጎደለ ፍላጎት ስለ አለው አለመሆኑን እናውቃለን። የሚዋጀውም የጎደለ ፍላጎት ስለ አለው አይደለም። የሚዋጀው፣ የሚፈጥረውና ማንኛውንም ነገር የሚያደርገው፣እራሱን ሊያከብር፣ባህርዩን ሊገልጥ ነው። ይህን በማድረግ በሰማያት ያሉ ፍጡራን ሁሉ፣ በምስሉ የተፈጠሩ ሰብዓዊ ፍጡራን ሁሉ፣ ክብሩን እንዲያንጸባርቁ የተመረጡ፣ ቅድስናውን እንዲሁም ክብሩን በማሳየት ባህርዩን እንዲገልጹ ነው። የሚያደርገውን ሁሉ የሚያደርገው፣ለዚህ ፍጻሜ ነው። ግን ለምንድነው የሚዋጀው? የሚዋጀው፣በተዋጀ ፍጥረት አማካኝነት ክብሩን ለመግለጥ እንዲችል ነው።(ዶር.ኬ. ኤሪክ ቶነስ)*

ሁለተኛ፣እግዚአብሔር ለፍጥረት ያለው ፍቅር ወልድ በመዋጀት ውስጥ በነበረው ሥራ የተነሳሳም ነው።

## ፍጥረት

ወልድ በመዋጀት ሥራ ውስጥ እግዚአብሔር ለፍጥረት ባለው ፍቅር የተነሳሳ መሆኑ በተለያዩ መንገዶች ተረጋግጧል። እንደፈጣሪነቱ ለፈጠረው ነገር ሁሉ በሚያደርገው ጥበቃ፣ በተለይም በአምሳሉ ለሠራቸው ሰብዓዊ ፍጡራን ባለው ፍቅር ይህን እንመለከታለን።

በጣም የታወቀው የዚህ ምሳሌ በዮሐንስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 16-18 ያለውና ቀጥሎ እንዳለው የሚነበበው ነው፡

> *"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ አግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከመስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና፣እግዚአብሄር ልጁን ወደ ዓለም የላከው በዓለም ለመፍረድ ሳይሆን፣ ዓለምን በእርሱ ለማዳን ነው። በእርሱ የሚያምን*

*ሁሉ አይፈረደበትም፣ በእርሱ የማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ፣ አሁኑኑ ተፈርዶበታል"(ዮሐንስ 3፡1618)*

ዮሐንስ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር የሚለውን ቃል በተለያዩ መንገዶች የተጠቀመበት መሆኑን ማመልከት አለብን:: በተለያዩ ቦታዎች ጽንፈ ዓለሙን፣ ምድርን፣ሰብዓዊ ፍጡራንን ሁሉ፣ብዙ ሰዎችን፣ እግዚአብሔርን የሚቃወሙ ሰዎችን፣ እና የሰብአዊ ሥርዓቶች ፋይዳዎችን እንዲሁም አሰራሮችን ለማመልከቻነት ተጠቅሞበታል:: በዚህ ሁኔታ፣ፍጥረትን አራሱን ወይም በፍጥረት ውስጥ ያለውን ሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ የሚያመለክት ይመስላል::

የዮሐንስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 16-18 መሰረታዊ ሀሳብ፣ እግዚአብሔር ዓለምን እንዲያድን ያደረገው፣ፍቅሩ መሆኑን መግለጽ ነው:: ዓለም አሁንም በአምሳሉ በተፈጠሩ፣ አገልጋዮቹ በሆኑ ሰብዓዊ ፍጡራን የተሞላችና የምትመራ፣ በክብሩ የተሞላች መንግሥቱ እንድትሆን ፈልጓል:: በመሆኑም የሰብዓዊ ፍጡራን አማኝ ቅሪቶችን እንዲያድን ልጁን ለመላክ አቀደ:: እግዚአብሔር ያመኑ ሰዎችን በማዳን አዲስ ሰው ይፈጥር ጀመር:: ከዚህ በኋላ ሰማያትንና ምድርን የክብሩ መገለጫ መንግሥትና፣ ነጻ የወጡ አዳዲስ ሰብዓዊ ፍጡራን መኖሪያ እንዲሆኑ ያድሳቸዋል:: ይህ ጉዳይ ሮሜ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 20-22፣2 ጴጥሮስ ምዕራፍ 3 ቁጥር13፣ እና ራእይ ምዕራፍ 21 ከቁጥር1-4 በመሳሰሉት ሥፍራዎችም ትምህርት ተሰጥቶበታል::
ሦስተኛ፣ እግዚአብሔር ለአማኞች ያለው ፍቅርም ወልድ በመታደግ ውስጥ የነበረውን ሥራ አነሳስትዋል::

## አማኞች

እግዚአብሔር አማኞችን የሚወድ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ክፍሎች ተገልፆአል:: ከእኛ ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዲኖረውና እንዲባርከን ይፈልጋል:: እኛም በአጸፋው እንድንወደውና፣ በግንኙነታችን ለዘለዓለም ደስ እንዲለንም ይሻል:: እንደውም፣ ከመወለዳችን በፊት እግዚአብሔር ያወቀንና የወደደን መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚነግረን፣ ለአማኞች ያለው ፍቅር በጣም የተለየ ነው:: ይህን ሮሜ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 29-39፣ ኤፌሶን ምዕራፍ 1 ከቁጥር 4-12፣እና 1 ጴጥሮስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 2 ውስጥ እንመለከታለን:: በተጨማሪም፣እግዚአብሔር ለአማኞች ያለው ፍቅር፣መታደግን እንዲያከናውን አብ ወልድን የላከበት ዓላማ ዋና ክፍል እንደነበርም መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ያደርጋል:: ወልድ የአብን ፍቃድ ለማከናወን ያለው ፍላጎትም ከዚህ ጋር ይጠቃለላል:: ይህ በተለይ ግልጽ የሚሆነው፣ዮሐንስ ምዕራፍ 16 ቁጥር 27፣

እና 1 ዮሐንስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 16፣ እንዲሁም ምዕራፍ 4 ከቁጥር 10-19 ውስጥ ዮሐንስ በጻፋቸው ጽሑፎች ነው።

እግዚአብሔር የሚያደርገው ነገር ሁሉ፣ ቢያንስ በከፊል ለህዝቡ ባለው ፍቅር የሚነሳሳ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ፍቅሩ ፍጹም በሆነ መንገድና ሙሉ በሙሉ የተገለጸውም ወልድ ውስጥ ነው። ሁላችንም በህይወት ትግል ውስጥ እናልፋለን፣ በመሆኑም አንዳንዴ እግዚአብሔር የሚወደን መሆኑን እንኳን እንጠራጠራለን። እግዚአብሔር ግን በምንታገልበት ወይም በምንጠራጠርበት ጊዜ፣ ለእኛ ያለው ፍቅር ከቀድሞው የቀነሰ አይሆንም። እውነቱ፣ ኀጢአታችንን እና ትግላችንን ሁሉ ቢያውቅም የሚወደን መሆኑ ነው። በእርሱ ባላመንበት ወይም ኀጢአታችንን ለመተው ባልፈለግንበት ጊዜ እንኳን፣ይዋጀን ዘንድ ልጁን እስከ መላክ ድረስ ወዶናል። ያ ደግሞ ግዙፍ ዋጋ የሚከፈልበት ነበር-ኢየሱስ ከባዱን ኀጢአታችንን ተሸክሞ መሰቃየትና መሞት ነበረበት። ለፍቅር ሲል አደረገው። አሁን ደግሞ በትንሣዔው፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው የመታደግ ፍቅር ሕያው ምስክር ሆነ።

የእግዚአብሔርን የመታደግ ዓላማ ከተመለከትን እንገዲህ፣መታደግን እውን ወደ አደረጉት መለኮታዊ ተስፋዎች እንሂድ።

### ተስፋዎች

የእግዚአብሔር ተስፋዎች አይለወጡም። በፍጹም ሊለወጡ አይችሉም፣ እርሱም በፍጹም አያፈርሳቸውም። እግዚአብሔር የሚሰጠውን ተስፋ በእርግጥ ይፈጽማል። ወልድ በመታደግ ውስጥ ስለ አለው ሚና ለሚኖረን ግንዛቤ ይህ ጠቃሚ ነው፣ ምክንያቱም፣መታደግ በአብና በወልድ መካከል ባሉት ተሰፋዎች ላይ ሥር የሰደደ ነው።

ቀደም ሲል በዚህ ትምህርት ውስጥ እንዳየነው፣የሥላሴ አካላት፣አንዳንድ ሰዎች "የመታደግ ቃልኪዳን" የሚሉትንና የወደቀውን ሰብዓዊ ፍጡር ለመታደግ ተሰፋ የሰጡበትን ስምምነት አደረጉ። ቀጥሎ የምንመለከተው፣ይህ የመታደግ ቃል ኪዳን፣በኀጢአት ከመውደቅ በኋላ፣በመገኘት ለይ ባለው ሌላ መዋጀት ውስጥ ውጤት ያስገኘበትን ሁኔታ ነው። የሥነ መለኮት ሰዎች፣ይህን በኋላ የሆነ ቃል ኪዳን፣ "የጸጋ ቃል ኪዳን" ይሉታል። ይህ የከበረ ማስተካከል በአንድ በኩል በአብ፣በሌላ ወገን ደግሞ በወልድ እንዲሁም በታደጉ ሰብዓዊ ፍጡራን መካከል የተደረገ ነው። እናም ከሰው በኀጢአት መውደቅ በመጀመር፣ ኢየሱስ በክብር በሚመለስበት ጊዜ እስከ ሚያበቃበት ድረስ፣ አጠቃላዩን የመታደግ ጊዜ ይገዛል።

በዚህ ቃል ኪዳን እግዚአብሔር አብ ለፍጥረት፣እና በልጁ በኩል፣ በተለይም በልጁ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ በኩል የመንግሥቱን እቅዶች እንደሚፈጽም ተስፋ ሰጥቷል። ወልድ ደግሞ፣ ከተመረጠው የዳዊት የዘር ሐረግ ከተወለዱ ነገሥታት ሥጋ የለበሰ ሰው ሆኖ ለመወለድና ከመዋጀት ተስፋ በፊት የተቀመጡ ግዴታዎችን ሁሉ ለመፈጸም ቃል ገባ። ለወደቀው የሰው ዘር በመስዋእትነት መሞትና፣ በንስሐ እንዲሁም በእምነት ወደ እርሱ የሚመለሱ ሁሉ አሁን ካለው ርኩሰትና የኀጢአት በደለኛነት መዋጀት ነበረባቸው። ከነዚህ ተስፋዎች ጋር በተያያዘ ሁኔታ፣ወልድ ለሚያድናቸው ሰዎች የድነትን ትሩፋቶች ያደርስ ዘንድ፣ መንፈስ ቅዱስን ለመላክ አብና ወልድ ተስማሙ።

የሥነ መለኮት ሰዎች፣የጸጋ ቃል ኪዳንን፣እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባውን የጸጋ ተስፋ ለማረጋገጥ በታሪክ ሂደት ባከናወናቸው የቃል ኪዳን ሥርዓቶች ላይ በመመሥረት በስድስት አተገባበሮች ይከፋፍላቸዋል። እነዚህ አተገባበሮች የቃል ኪዳኑ ሥርዓት በሚከናወንበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከመሩ ሰብዓዊ ፍጡራን ጋር የተገናኙ ናቸው።

ይህ የጀመረው፣ ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ውስጥ ነው፣ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ ዋና የሆነው አዳም እንደ ወደቀ ወዲያው። በተለምዶ ይህ የቃል ኪዳን "አዳማዊ አተገባበር" ወይም በቀላሉ፣"አዳማዊ ቃል ኪዳን" በመባል ይታወቃል። በዚህ አተገባበር ሥር፣ ድነት ለሰብዓዊ ፍጡር መጀመሪያ የተሰጠው፣ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ቁጥር 15፣ ቀደም ብለን፣"የመጀመሪያው ወንጌል" ባልነው ውስጥ ነው። ቀጣዩ፣ዘፍጥረት ከምዕራፍ 6-9 ባለው ክፍል ከኖህ ጋር የተደረገው የመታደስ ቃል ኪዳን ነው። በኖሃዊው የቃል ኪዳን አተገባበር፣የወልድ የመዋጀት ሥራ እስኪፈጸም ሰብአዊው ፍጡር እንዲኖር ፍጥረትን በተረጋጋ ሁኔታ ለማቆየት እግዚአብሔር ቃል ገባ።

ይህን ተከትሎ፣ እግዚአብሔር ከአብርሐም ጋር አንድ ቃል ኪዳን አደረገ፣ ዘፍጥረት ምዕራፍ 15 እና 17 ውስጥ የተገለጸውንና፣ ዘፍጥረት 22 ውስጥ እንደገና የተረጋገጠውን። ይህ ቃል ኪዳን ለአብርሐም ቤተሰብ ልዩ ዕድል እና ግዴታን በመስጠት፣ ከልጅ ልጆቹ አንዱ ታዳጊ እንደሚሆን ቃል ገባ። በገላትያ ምዕራፍ 3 መሠረት ይህ ልዩ የልጅ ልጅ፣ኢየሱስ ነበር።

ጳውሎስ ገላትያ ምዕራፍ 3 ቁጥር 16 ውሰጥ የሚለውን ተመልከቱ፣

> *የተስፋውም ቃል የተነገረው ለአብርሐምና ለዘሩ ነበር፣ መጽሐፍ ለብዙ ሰዎች እንደሚናገር፣ "ለዘሮቹ" አይልም፣ ነገር ግን ለአንድ ሰው እንደሚናገር "ለዘርህ" ይላል፣ እርሱም ክርስቶስ ነው።(ገላትያ 3፡16)*

የአብርሃማዊው ቃል ኪዳን ተስፋዎች አተገባበር የተሰጠው፣ ለአብርሃም ብቻ ሳይሆን፣ለክርስቶስም መሆኑን ጳውሎስ ተገንዝቧል። የእግዚአብሔር ልጅ፣ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን በረከቶች ሁሉ፣በተለይም ከኀጢአት የመዋጀት በረከትን፣ ለታማኝ ሕዝቦቹ ለማምጣት ተስፋ የተደረገበት ታዳጊ ነበር።

ቀጥሎ የመጣው፣ በሙሴ ጊዜ ከእስራኤል ጋር የተደረገው ቃል ኪዳን ሲሆን፣ከዘጸአት 19-24 ባሉት ክፍሎች እና ዘዳግም መጽሐፍን በመሳሰሉት ክፍሎች የተገለጸው ነው። በሙሴያዊው ቃል ኪዳን ትግበራ፣ ወይም "በሙሴያዊው ቃል ኪዳን" ውስጥ፣ እግዚአብሔር፣ ወልድ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርቶስ ሆኖ ሥጋ በሚለብስበት ጊዜ፣ በመጨረሻ ያደረገውን መስዋእትነት የገለጠውን መስዋዕታዊ ሥርዓት መሠረተ። እነዚህ ሙሴያዊ መስዋእቶች፣አብና ወልድ ከፍጥረት በፊት ያደረጉዋቸው ተስፋዎች ግለጽ ማረጋገጫዎች ነበሩ። በመሆኑም የእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝቦች በነዚህ መስዋዕቶች በኩል፣ወልድ በመጨረሻ የሚያከናውነውን መታደግ ቅምሻዎች አግኝተዋል።

በዚህ ጊዜ ነው እስራኤል እንደ የንጉሥ ካህንና ቅዱስ ሕዝብ የተመሠረተችው። ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን በመታዘዝ፣በመጨረሻ ወልድ የሚመራውን ምድራዊ መንግሥት መመሥረት ነበረባቸው።

የቃል ኪዳኑ አምስተኛ አተገባበር እና፣ በብሉይ ኪዳን ጊዜ የመጨረሻው ትግበራ፣በዳዊት ሥር የነበረውና ብዙ ጊዜ "ዳዊታዊ ቃል ኪዳን" የሚባለው ነው። ዳዊታዊው የጸጋ ቃል ኪዳን ትግበራ፣2 ሳሙኤል ምዕራፍ 7 እና መዝሙር 89 እንዲሁም 132 በመሳሰሉት ዕፍራዎች ተጠቅሷል። በዚህ ጊዜ፣ የሚዋጀው ከዳዊት ዘር እንደሚወጣ፣የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ምድር እንደሚያመጣ፣ በጽድቅ በተሞላው አገዛዙ አማካይነትም፣ በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ ድነትን እንደሚያመጣ እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቶ ነበር።

በመጨረሻም፣ስድስተኛው ትግበራ በኢየሱስ ጊዜ የጀመረ ሲሆን፣እስኪመለስ ድረስ ይቀጥላል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ትግበራ፣"አዲሱ ቃል ኪዳን" ይለዋል። ሉቃስ መዕራፍ 22 ቁጥር 20፣ እና ዕብራውያን 9 ቁጥር 15 እና ምዕራፍ 12 ቁጥር 24 በመሳሰሉት ስፍራዎች እንደምንመለከተው። በዚህ የጸጋ ቃል ኪዳን አስተዳደር ሥር፣የመዋጀት ሥራ ሁሉ፣ይፈጸም ነበር፣ አሁንም በመፈጸም ላይ ነው። ኢየሱስ የኀጢአት መስዋእት ሊሆን በተስፋ የተሰጠ ሚናውን ፈጽምዋል። መስዋእቱን አብ ተቀብሎታል። መንፈስ ቅዱስም፣ እንደ አዳኛቸው አድርገው በኢየሱስ ለሚያምኑ ሁሉ ድነትን በመተግበር ላይ ነው።

*የድነት መሰረቱ ሁልጊዜ ወልድ ነው። ከኢየሱስ አገልግሎት አንጻር በድነት ታሪክ ውስጥ በቅደም ተከተል ያላችሁበት ቦታ ወደ ኋላ መለስ ተብሎ በሚታይበት ጊዜ፣ ያ ትኩረት ወይም እይታ ያለበትን ሥፍራ ይወስነዋል። በአዲስ ኪዳን ባለነው በእኛ ሁኔታ፣ በኢየሱስ አገልገሎቶች የተፈጸሙና የተከናወኑ ትንቢቶችን ወደ ኋላ መመልከት ማለት ነው። ወይም ዛሬ እንዳለን ግንዛቤ፣በአዲስ ኪዳን ዘመን የነበሩ ሰዎች በጣም ግልጽ በሆነ መንገድ ባይመለከቱም፣ ይህን ከሚወስነው የእግዚአብሔር ተስፋ ጋር በሚስማማ ሁኔታ በኢየሱስ ክርስቶስ በተከናወኑት ሥራዎች ተፈጽመዋል። አዎ የድነታችን መሠረቱ ምንጊዜም ኢየሱስ ነው።(ዶር. ሮብ ሊስተር)*

*ክርስቶስ ሳይመጣ በፊት ሰዎች የዳኑባቸው የተለያዩ መንገዶች ኖረው ይሆን? የሚሉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። እናም ቀጥሎ ያሉትን የመሳሰሉ መልሶች በመሰጠት ላይ ናቸው፣አንዳንዶች ምናልባት በመንግሥት በኩል፣አንዳንዶች በሕጉ በኩል፣አንዳንዶቹ ደግሞ ምናልባት በሌሎች ሁኔታዎች፣ ወይም በደንብና የእስራኤል ሕዝብ አካል በመሆን። አንዳንዶች ምናልባት በመገረዝ አማካይነት ድነው ይሆናል። አጠቃላዩ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ግን፣እነዚህ ሁሉ ነገሮች በትክክል የሚያድነን አንድ ሁነት ዝግጅቶች መሆናቸውን ነው የሚያስረዳው። የመስዋእቱ ሥርዓት በዝርዝር የሰፈረ ቢሆንም እና፣ አስፈላጊ ነገር ቢሆንም እንኳን፣ነቢያቱ ራሳቸው ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር የተመለሰ ልብ ከሌለው፣መስዋእት ማቅረቡን እንዲያቆም ይነግሩት ነበር። ከዚያ ወዲህ ደግሞ፣ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኀጢአትን እንደማያስወግድ የዕብራውያን መጽሐፍ በግልጽ ያስረዳል። ይህን የሚያደርግ አንድ መስዋእት ብቻ ነበር የነበረው። ይህ የሆነው ደግሞ በክርስቶስ ልዩ መሆን ነው። እርሱ እግዚአብሔርና ሰው በአንድ አካል ነው። የዚህ አካል ተናጠል መሆን፣ ለእግዚአብሔር ሊዋጀን የሚችል ብቸኛ አካል መሆኑ ነበር(ዶር.ቶማስ ኔትልስ)*

ፍጥረትን በተመለከተ የመለኮትን ዓላማና ተስፋ ከተረዳን እንግዲህ፣ወልድ መዋጀትን ለመፈጸም ያከናወነውን ሥራ፣ በተለይም እንደ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሥጋ በመልበሱ በኩል፣የሠራውን እንመረምራለን።

## ሥራ

የኢየሱስን የመታደግ ሥራ አራት ገጽታዎች እንመለከታለን፣የእግዚአብሔርን መንግሥት ማወጁ፣ለአብ መታዘዙ፣ትንሣኤው፣እና እርገቱ። በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማወጁን እንመልከት።

### የመንግሥት መምጣት

በብሉይ ኪዳን ጊዜ ሁሉ፣ የእግዚአብሔር ሕዘቦች፣እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ፍጹም በማጥፋት በአስገራሚ ሁኔታ መንግሥቱን ወደ ምድር እንዲያመጣና፣ በዘላለማዊ በረከት እንዲመሠረቱ የሚያደርግበትን ዕለት በጉጉት ይጠባበቁ ነበር። ይህ ዕለት ነበር ለሰብዓዊ ፍጡር መጀመሪያ የተሰጠው ሥልጣን በመጨረሽ የሚከናወንበት። እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሙሉ በሙሉ ወደ ነበረበት ሁኔታ በመመለስ እና፤በሰማያት እንደሆነው ሁሉ ፍቃዱ በምድር እንዲሆን በማድረግ ላይ ነበር።

የብሉይ ኪዳን ነቢያት ስለ እስራኤል እንደገና ወደ ነበረበት ሁኔታ መመለስ፣ስለ ሰብዓዊ ፍጡርና ፍጥረት ባጠቃላይ በተናገሩበት ጊዜ፣ጉዳዩን ብዙ ጊዜ የጌታ ቀን ወይም የመጨረሻው ጊዜ ብለውታል። መሲሑን ወይም ደግሞ በመጨረሻው ጊዜ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚመራ ዋና አካል ነው ብለዋል። በአዲስ ኪዳን ገለጻ መሠረት ደግሞ፣ ኢየሱስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ላይ ለመመሥረት የመጣና ለብዙ ዘመን የተጠበቀ መሲሕ ነው።

ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ፣የእግዚአብሔርን መንግሥት ያመጣ መሆኑን አስተምሯል። ለምሳሌ፣ ማቴዎስ 12 ቁጥር 28 ውስጥ፣ "የእግዚአብሔር መንግሥት ወደእናንተ መጥታለች" ብሏል። ማለት፣ያኔ መንግሥቱ እዚያው ነበር። ሉቃስ ምዕራፍ 16 ቁጥር 16፣ "ሰውም ሁሉ ወደዚያ ለመግባት ይሻማል" ባለ ጊዜ፣ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በመግባት ላይ መሆናቸውን እንደገና አስተምሯል።

የሚያሳዝነው ነገር፣ በኢየሱስ ጊዜ የነበሩ ሰዎች፣የእግዚአብሔር መንግሥት መጥቷል የሚለውን ሃሳብ አልተቀበሉትም፣ምክንያቱም፣ ሰዎች ሁሉ የሚመለከቱት የማይታበልና መላውን ምድራዊ ሥርዓት የሚያስወግድ ግልጽ፣ እንዲሁም አካላዊና ምድራዊ እውነት እንደሚሆን ጠብቀው ነበር። ኢየሱስ ግን፣መንግሥተ ሰማይ በተለየ መንገድ መጥቶ እንደ ነበር አስተምሯል። ሉቃስ ምዕራፍ 17 ቁጥር 20 እና 21 ውስጥ የተናገረውን ተመልከቱ፣

*"የእግዚአብሔር መንግሥት በሚታዩ ምልክቶች አትመጣም፣ ሰዎችም እዚህ ነው ወይም እዚያ ነው ማለት አይችሉም፣ እነሆ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና"(ሉቃስ 17፡20-21)*

እርግጠኛ ለመሆን፣ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት በሙሉነቱ አላመጣም። ሥራውን ብቻ ነው የጀመረው። በመሆኑም፣ የጀመረውን እንዲጨርስ በመጠባበቅ ላይ ነን-የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲፈጽም ወይም ዳር እንዲያደርስ። ሂደቱ ግን ዝግ ያለ ነው። ኢየሱስ ማቴዎስ ምዕራፍ 13፣ማርቆስ ምዕራፍ 4 እና ሉቃስ ምዕራፍ13 ውስጥ በሚገኙት ምሳሌዎቹ እንዳስተማረው፣የእግዚአብሔር መንግሥት፣ በጊዜ ሂደት እንደ ሚያድግ ዘር ወይም በጊዜ ሂደት ኩፍ እንደሚል የዳቦ ሊጥ ነው። ከነዚህ ምሳሌዎች በሚገኛኝ ሁኔታ፣የእግዚአብሔር መንግሥት ተዘርቷል፣ኢየሱስ እስኪመጣ ግን ፍሬው አይሰበሰብም ልንል እንችላለን።

ኢየሱስ፣ሥጋ የለበሰው የእግዚአብሔር ልጅ፣የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ምድር ማምጣቱን አዲስ ኪዳን ያስተምራል። በክብር የሚመለስበትን ጊዜ፣ይህ ክፉ ጊዜ ፍጹም የሚያበቃ መሆኑን እንዲሁም አዲሱ ሰማይና አዲሱ ምድር ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ፍጹም በሆነ መንገድ ወደ ነበሩበት የሚመመለሱበትን ሁኔታ የሚያመጣ መሆኑንም አዲስ ኪዳን በእርግጠኛነት ያስተምራል። ይህ ትልቅ ተስፋ እና እርግጠኛነትን ሊያሳድርብን ይገባል። በወደቀው ዓለም ውስጥ፣ አንዳንድ ጊዜ ክፉው አሠራር የሚያሸንፍና እኛም በከንቱ የምንሰቃይ ይመስላል። እግዚአብሔር ግን ጽድቅን ወይም ፍትህን ለዘላለም አያዘገይም። በጠላቶቹ ላይ የመጨረሻ ፍርድ የሚሰጥበት ጊዜ በመምጣት ላይ ነው። ኀጢአትን፣ስቃይንና ሞትን ሙሉ በሙሉ ከዓለም ያጠፋል። ታማኝ ለሆኑት ሕዝቦቹ ሁሉም በመንግሥቱ ውስጥ ዘላለማዊ ውርስ ይሰጣቸዋል። ኢየሱስ በብዙ ተዓምራትና በማስተማር፣ማንነቱን አረጋግጧል፣ከዚያም በላይ፣ለመንግሥቱ በረከቶች መያዣ እንዲሆነንም መንፈስ ቅዱሱን ሰጥቶናል። ስለዚህ፣የመንግሥቱን መምጣት ወደ ፍጻሜው ለማድረስና ሙሉ ውርሳችንን ሊሰጠን እንደሚመለስ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን።

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ያመጣበትን ሁኔታ ከተመለከትን እንግዲህ፣ ለአብ ታዛዥ የሆነበትን ሥራውን እንይ።

## ታዛዥነት

በትምህርታችን መጀመሪያ ላይ፣ሰብዓዊ ፍጡር በኀጢአት በመውደቁ ምክንያት የመጣውን ግላዊ ውጤት ተመልክተናል። አዳም እንደ ቃል ኪዳን እራስነት ሰብዓዊ ፍጡርን ሁሉ በመወከሉ፣የእርሱ የመጀመሪያ ኀጢአት በደለኛነት ወደ ሰው ሁሉ መተላለፉንም ተመልክተናል። ከእግዚአብሔር ጋር የነበረን ሕብረት በመቋረጡ፣ ለራሳችን ድነት የምናገኝበትን ሁኔታ አጣን።

በጣም ጠቃሚ በሆነ መንገድ ስናስብ ኢየሱስ እንደ አዳኛችን የሠራው ሥራ፣አዳም ያልቻለውን ሥራ ማከናወንንም አካቷል። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞቱ ያበቃና ለአብ ፍጹም ታዛዥ የሆነ ህይወት ነው የኖረው። በታዛዥነቱም አዳም ያጣቸውን በረከቶች አገኘ። አሁን እነዚያን በረከቶች፣ታማኞች ከሆኑ ህዝቦቹ ሁሉ ጋር ይካፈላል። ጳውሎስ ሮሜ ምዕራፍ 5 ከቁጥር12-19 ባለው ክፍል በኢየሱስ እና በአዳም መካከል ስላሉት መመሳሰሎች በሰፊው ተናግሯል። እንደውም፣ 1 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15 ቁጥር 45 ውስጥ

"የመጨረሻው አዳም" ብሎታል።

ኢየሱስ በምድራዊ ህይወቱ ሁሉ የፈጸመውን ታዛዥነት በተመለከተ፣ የሥነ መለኮት ሰዎች ስለ ሁለት ነገሮች ይናገራሉ። በአንድ በኩል፣ የመሰጠት ታዛዥነቱ፣ ለመስዋዕትነት ላበቃው የውርደትና የስቃይ ህይወት መገዛቱ ነበር። የመስቀል ላይ ሞቱ፣ ኀጢአት በመስቀል ላይ ይቀጣ የሚለውን የእግዚአብሔር ጻድቅ ጥያቄ አርክቷል። ኢየሱስ በመሰጠት ታዛዥነቱ የኛ ምትክ ነበር። በደላችን በእራሱ ላይ እንዲሆን፣ማለት እዳው እንዲሆን ፈቀደ። በዚሁ መሰረት በእግዚአብሔር ዐይን በደለኛ ስለሆነ፣በእኛ ሥፍራ ሞተ። ይህ አንድ ስራ የኀጢአታችንን ቅጣት ከፈለ። በመሆኑም፣ የእግዚአብሔር ፍርድ እና ቁጣ ከእንግዲህ አያስፈራንም። ይህ ሥራ ለኀጢአታችን ይቅርታን አስገኝቶ ከሕግ ቅጣት ነጻ አድርጎናል።

ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 5 ቁጥር 18 እና 19 ውስጥ እንደ ጻፈው፣

> *"ከእንግዲህ በአንድ ሰው መተላለፍ የተነሳ ኩነኔ በሁሉ ሰው ላይ እንደመጣ፣ እንዲሁም በአንዱ የጽድቅ ሥራ ለሰው ሁሉ ህይወትን የሚሰጥ ጽድቅ ተገኘ። በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኀጢአተኞች እንደሆኑ፣በአንዱ ሰው መታዘዝ ደግሞ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ። "(ሮሜ 5፡18-19)*

እዚህ ላይ ጳውሎስ፣አዳምንና ኢየሱስን አነጻጽሯል። የሚገልጸው ነገር፣አዳም በአንድ ወቅት ይወክለን እንደነበረ ኢየሱስ ስለሚወክለን፣የእርሱ የመስቀል ላይ

መስዋእትነት፣ ከእግዚአብሔር ጻድቅ ፍርድ ነጻ አድርጎ፣እንደ ጻድቃን እንዲያየን ያደርገዋል።

ኢየሱስ የፈጸመው ሁለተኛ ዓይነት መታዘዝ፣ተግባራዊ መታዘዝ ነው። ይህ አብ ለሚያዘው ማንኛውም ነገር የመታዘዝ ህይወቱ ነበር። ሥጋ በለበሰበት ሁኔታ፣ የእግዚአብሔርን ሕግ በፍጹም ሁኔታ ጠብቋል። ኀጢአት አልሠራም፣ሁል ጊዜ እግዚአብሔር ያዘዘውን አደረገ። በተመሳሳይ ሁኔታ በደላችንን በመስቀል ላይ ኢየሱስ እንዲሸከመው ስለተደረገ፣የእርሱ ጻድቅ መታዘዝ ወደ እኛ ተላልፏል። ሥነ መለኮታውያን ብዙ ጊዜ እንደሚሉት፣ ምንም እንኳን በውስጣችን ካለው ኀጢአት ገና ሙሉ በሙሉ ነጻ ባንሆንም ጻድቃን ተብለናል። እግዚአብሔር ወደ እኛ የሚመለከተው፣ሥጋ የለበሰ ልጁን ኢየሱስን እንደሆንን አድርጎ ነው፣ የእርሱን ፍጹም የሆነ ህይወት እንደ ኖርን፣ የእርሱን መልካም ሥራዎች ሁሉ እኛ እንደፈጸምን አድርጎ። በመሆኑም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረን ሕብረት እንደገና ተመሠረተ። ምንም እንኳን የውርስ ኀጢአት ድነትን በራሳችን ሥራ ከማግኘት በያግደንም፣ኢየሱስ ከፈጸመው ሥራ የተነሣ እግዚአብሔር የድነትን በረከት ይሰጠናል።

> *ከኀጢአተኛነትና ከወደቀው ሁኔታችን ለመውጣት፣እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው "ከቁጣ ልጅችነት" ነጻ ለመሆን፣እግዚአብሔር ችግራችንን እንዲፈታልን ያስፈልገናል። ረዳትና ተስፋ የሌለንና፣የራሳችንን የኀጢአት ችግር ለመፍታት የማንችል ነን። እግዚአብሔር ግን በጸጋው ችግራችንን ይፈታልናል። ይህን የሚያደርግበት መንገድ እንዲወክለን ልጁን በመላክ ነው። እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆኖ ፍጹም የሆነ የታዛዥነት ህይወት ኖረ፣ በመስቀል ላይ ፍጹም ሞት ሞተ፣ሞትን ለእኛ ድል በማድረግ፣ ከመቃብር ተነሣ። እናም ድነት የምናገኝበት ብቸኛ መንገድ፣ ኢየሱስ የሚወክለው የዚህ አዲስ ፍጥረት፣ነጻ የወጣውና ትንሣኤ ያገኘው የመጀመሪያ ፍሬ አካል መሆን ነው። የዚህ ነገር አካል የምንሆንበት መንገድ፣በአዲሱ ሰው፣በአዲሱ አዳም፣ከወደቀ ሁኔታው ነጻ የወጣውን ሰው በወከለው በክርስቶስ በማመን ነው። ስለዚህ፣ድነት የምናገኘው፣ በክርስቶስ፣ሰውም አምላክም በሆነው፣በመታደግ ሥራው በሚወክለን በእርሱ በማመን ነው።(ዶር.ኬ.ኤሪክ ቶማስ)*

የእግዚአብሔርን መንግሥትና መታዘዝን በተመለከተ የኢየሱስን ሥራ ከተመለከትን እንግዲህ፣ ከሞት መነሣቱን ወደ መመልከቱ መለስ እንበል።

## ትንሣኤ

የኢየሱስ አካላዊ ትንሣኤ፣ ለማዳን ሥራው ወሳኝ ነው። ከሞት በመነሣት፣ ሞትን አሸንፎ ፣በእርሱ ለሚያምን ሁሉ የዘላለማዊ አካላዊ ትንሣዔ ዋስትና አስገኘ።

ጳውሎስ በ1 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15፣ቁጥር 20 እና 21 ውስጥ የኢየሱስን ትንሣኤ የገለጸበትን ሁኔታ ተመልከቱ፣

> *"ነገር ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት ሁሉ በኩራት ሆኖ በእርግጥ ከሙታን ተነስቶአል። ሞት በአንድ ሰው በኩል እንደመጣ የሙታንም ትንሣኤ በአንድ ሰው በኩል ሆኖአል"(1ቆሮነቶስ 15:20-21)*

የአዳም ኀጢአት ሞት አመጣ። ኢየሱስ ከሞት በተነሣ ጊዜ ግን፣ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ ከሞት እንደሚነሱ ዋስትና ሰጠ። በመሆኑም በሚመለስበት ጊዜ አዳኛችንን በሚመስል የከበረ አካል ለዘላለም እንኖራለን።

ይህን የኢየሱስ ትንሣኤ መረዳት በአዕምሯችን ይዘን፣ ወደ አራተኛውና የትነሣኤ ሥራው ወደ ሆነው ጉዳይ እንሂድ፣ወደ ሰማይ ወደ ማረጉ።

## እርገት

ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ፣ለአርባ ቀናት ያህል ለደቀመዛሙርቱ እየተገለጠ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት አስተምሯቸዋል። ይህ ጊዜ እንደ አበቃም በአካል ወደሰማይ ተወሰደ። ይህ ሁነት ሉቃስ ምዕራፍ 24 ቁጥር 50 እና 51፣ እንዲሁም ሐዋ. ምዕራፍ 1 ከቁጥር 3-11 ባሉት ክፍሎች ተመዝግቧል።

ትንሣኤው፣ለኢየሱስ የማዳን ሥራ ጠቃሚ ነበር፣ቢያነስ ለሁለት ምክንያቶች። በአንድ በኩል፣ወደ ሰማይ ያረገው፣እንደ ንጉሥ ዙፋን ላይ ለመቀመጥ ነው። አሁን፣በፍጥረት ሁሉ ላይ፣በተለይ በሕዝቡ እና በቤተክርስቲያን ላይ እንደ አብ አገልጋይ ንጉሥ በመምራት ላይ ነው። እነዚህ ዝርዝሮች 1 ቆሮነቶስ ምዕራፍ 15 ከቁጥር 23-25፣ዕብራውያን ምዕራፍ 12 ቁጥር 2፣ እና 1ጴጥሮስ ምዕራፍ3 ቁጥር 22ትን በመሳሰሉ ሥፍራዎች ተጠቅሰዋል።

በሌላ በኩል፣ ትንሣኤው ኢየሱስ መሰዋእትነቱን በሰማያዊው ቤተመቅደስ እንዲፈጽምና፣ ለሕዝቡ በመማለድ እንዲሁም በማስታረቅ በአብ ዘንድ

እንዲሆን ስለሚፈቅድለትም እርገቱ ጠቃሚ ነበር። ኢየሱስ በመማለድ ሥራው፣አብ ይቅርታ ማድረጉንና ታማኝ ሕዝቡን መባረኩን እንዲቀጥል፣ በመስቀል ላይ ስለ ፈጸመው መስዋዕትነት ለአብ ያስታውሳል። ስለ እነዚህ ነገሮች ዕብራውያን ምዕራፍ 7 ቁጥር 25 እና ምዕራፍ 9 ከቁጥር 11-28 በመሰሉት ስፍራዎች እናነባለን።

እንግዲህ፣ በአንድ ሁኔታ፣ ከፍጥረት በፊት ወልድ ከአብ ጋር በፈጸመው የድነት ቃል ኪዳን ምክንያት፣ ሁል ጊዜ አማላጃችን ነው። ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ግን በተለየ ሁኔታ አስታራቂያችን ሆኗል።

ኢየሱስ እንደ አማላጃችን ያለውን ሚና ጳውሎስ በ1 ጢሞቴዎስ መዕራፍ 2 ቁጥር 5 እና 6 ውስጥ የገለጸውን ተመልከቱ፡

> *አንድ እግዚአብሔር አለና፣ ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ አስታራቂ አለ፣እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ራሱንም ለሰዎች ሁሉ ቤዛ አድርጎ ሰጠ፣ይህም በትክክለኛ ጊዜ ተመስክሮለታል (1 ጢሞ. 2፡5-6)።*

ኢየሱስ ክርስቶስ፣ሥጋ የለበሰው የእግዚአብሔር ልጅ፣ ለኀጢአተኞች በመስዋዕትነት ሞተ። እናም አሁን፣ በመስቀል ላይ የከፈለውን ቤዛነት በማያቋርጥ ሁኔታ ለነፍሳችን የሚውል መሆኑን እያረጋገጠ በአብ ዙፋን ፊት ያገለግላል።

ዕብራውያን ምዕራፍ 7 ቁጥር 25 ውስጥ እንዲህ የሚል ቃል አናነብባለን፣

> *ስለዚህ ስለ እነርሱ እየማለደ ሁልጊዜ በሕይወት ስለሚኖር፣በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል (ዕብ. 7፡ 25)።*

> *ወልድ በሆነው ኢየሱስ በቀር፣ ድነት በማንም የለም። ከሁሉ በፊት፣ ከሃይማኖት መሪዎች፣ ማናቸውም ፍጹም ወደ ሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን አልደረሱም፣ ማናቸውም ዘላለማውያን አይደሉም። ከዚህም በላይ ኢየሱስ በእግዚአብሔርና በሰው መሀል ብቸኛውና ብቁው አስታራቂ መሆኑ በጣም ጠቃሚ ነው። የዚህ ዓለም ሃይማኖተኞችና ፈላስፋዎች፣ጥሩ የህይወት መርህ ሊሰጡን ይችላሉ። ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣና ወደ እግዚአብሔር የሚመለስ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ*

*ብቻ ነው። እርሱ ብቻ ነው ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቀንና የእኛ ምትክ ሆኖ ኀጢአታችንን ሊወስድ የሚችል። በዚህ ሁኔታ ነው በእግዚአብሔርና በሰዎች መሀል አስታራቂ የሆነው። በሥነ ምግበራዊና በፍልስፍናዊ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በእርሱነቱ። በመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጥ፣ ብቸኛው ሰው የሆነ እግዚአብሔርና ሰብዓዊ ፍጡራንን የሚታደግ ኢየሱስ ነው። ማንም በግል ጥረትና በሥነ ምግባራዊ ጸባይ ወደዚህ ፍጹም ደረጃ ሊደርስ አይችልም።(ዶር. ስቴፈን ቻን)*

በህይወት ውስጥ በፈተናና በትግል ውሰጥ እናልፋለን። አንዳንድ ጊዜ እንደውም እግዚአብሔር ጸሎታችንን ስለ መስማቱ እንኳን እንጠራጠራለን። ነገር ግን፣ጥርጣሬያችን ቢኖርም፣ ኢየሱስ ከኀጢአት የሚቤዠንን ዋጋ ለመክፈል መሞቱን መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልናል። ዘላለማዊ ህይወትን ሊያረጋግጥልን ከሞት ተነስትዋል። ለእኛ ጥቅም መንገሥቱን ሊመራና የማያቋርጥ ምልጃ ሊያደርግልን በሰማይ ወደ አለ ዙፋኑ አረግ።

እንዲህ ሲባል፣ ህይወት ሁል ጊዜ ቀላል ናት ማለት አይደለም። ለማለት የተፈለገው፣ ታዳጊያችን ሁል ጊዜ ይሰማናል፣ያዝንልናል፣ይወደናል፣እርሱ ባመጣው ድነት ውስጥ ዋስትና ያለን መሆኑን ያረጋግጥልናል ማለት ነው።

በዘላለም፣ በፍጥረትና በመታደግ ውስጥ የኢየሱስን ሥራ ከተመለከትን እንግዲህ፣የመጨረሻውንና ዋናውን ጉዳይ በወደፊቱ የሰማያትና የምድር ፍጻሜ፣ የታዳጊያችንን ሥራ ለመመልከት ዝግጁ ነን።

## 5. ፍጻሜ

የሰማያትና የምድር ፍጻሜ፣በኢየሱስ ወደፊት የመመለስ ጊዜ ወዲያውኑ በዙሪያው የሚከናወኑ ሁነቶችንና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለዘላለም የሚቀጥለውን የድነታችንን የመጨረሻ ደረጃ ሁነቶች ያካትታል። የእግዚአብሔር ጠላቶች መውደም፣ የሕዝቦቹ የመጨረሻ በረከት፣እና የተዋጁ ሕዝቦቹ ለዘላለም የሚኖሩበትን እራሱን ተፈጥሮን ማደስን ይጨምራል። በአጭሩ፣ዓለም በመጨረሻ የከበረ የእግዚአብሔር መንግሥት የምትሆንበትን ጊዜ ይሆናል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰማያትና ምድር ፍጻሜ የሚገልጠውን በሦስት ደረጃዎች እንመረምራለን። በመጀመሪያ፣ የኢየሱስን መመለስ እንገልጻለን። ሁለተኛ፣ሰማያትንና ምድርን ወደ ፍጻሜ የሚወስዱ ተመሳሳይ ሁነቶችን

እንገነዘባለን። ሦስተኛ፣ የፍጻሜን ዘላለማዊ ውጤቶች እንገልጻለን። በኢየሱስ መመለስ እንጀምር።

**የኢየሱስ መመለስ**

የኢየሱስ መጀመሪያ በምድር መገለጥ፣አጅግ ትልቅ ትህትና ነበር። በአብዛኛው የዓለም ክፍል በሰፊው የታወቀ አልነበረም። በኖረባቸው ሥፍራዎች የነበሩ ዓለማውያን የታሪክ ሰዎች እንኳዋን ስለ እርሱ የተናገሩት ትንሽ ነው። ዳግም ምጽዓቱ ግን በጣም የተለየ ይሆናል።

ኢየሱስ ማቴዎስ ምዕራፍ 24 ቁጥር 30 ውስጥ እንዳለው፣

> *"የሰው ልጅም በሰማይ ደመና ሆኖ በሀይልና በታላቅ ክብር ሲመጣ ያዩታል"(ማቴ.4:16)*

እና ጳውሎስ በ1 ተሰሎንቄ ምዕራፍ 4 ቁጥር 16 ውስጥ አንዳለው፣

> *"ጌታ ራሱ በታላቅ ትእዛዝ፣ በመላእክት አለቃ ድምጽና፣ በእግዚአብሔር የመለከት ድምጽ ከሰማይ ይወርዳል"(1 ተሰ. 4:16)*

እነዚህና ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች፣ኢየሱስን መመለስ በተመለከተ ቢያንስ አራት ዝርዝር ነገሮችን ያመለክታሉ። መጀመሪያ አመጣጡ ግላዊና አካላዊ ይሆናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ወደዚሁ አሁን ወደ ምንኖርበት ዓለም ይመለሳል። ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1 ቁጥር 11፣ጌታ ወደ ሰማይ ባረገበት በዚያው ሁኔታ፣የሚመለስ መሆኑን ጨምሮ በዝርዝር ይገልጻል።

ሁለተኛ፣አመጣጡ ግልጽና የሚታይ ይሆናል። ሰው ሁሉ ያየዋል፣አመጣጡ በዓለም አቀፋዊ የእግዚአብሔር መለከትና በሊቀ መላእክት ድምጽ ይታወጃል።

ሦስተኛ፣የኢየሱስ ዳግም ምጽዓት በድል ይሆናል። እንደ ኃያል ንጉሥ ይመለሳል። ማቴዎስ ምዕራፍ 16 ቁጥር 27፣ ምዕራፍ 24 ቁጥር 31፣እና ምዕራፍ 25 ቁጥር31 በመሳሰሉት ምንባቦች ገለጻ መሠረት በመላእክት ሠራዊት ይታጀባል።

አራተኛ፣የኢየሱስ ክርስቶስ አመጣጥ ቅጽበታዊ እንደሚሆን የእግዚአብሔር ቃል ይገልጻል፣በምንጠብቀው ጊዜም አይመጣም። እንደውም፣በማቴዎስ ምዕራፍ 24 ቁጥር 36 መሰረት፣የዳግም ምጽዓቱ ቀን የሚታወቀው በአብ ብቻ ነው። ስለዚህ፣ አማኞች፣ ክርስቶስ ነኝ፣ወይም እርሱ የሚመለስበትን ቀን እናውቃለን የሚሉትን በፍጹም እንዳያምኑዋቸው።

ይህን የኢየሱስ ዳግም ምጽአት ግንዛቤ በአዕምሯችን ይዘን፣በፍጻሜው ጊዜ ኢየሱስ እንዲከናወኑ የሚያደርጋቸውን ሁነቶች እንመልከት።

## ሁነቶች

ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ ቢያነስ፣ ሦስት ወሳኝ ሁነቶች ይከናወናሉ፣ አጠቃላዩ ትንሣኤ፣ የመጨረሻው ፍርድ፣እና የፍጥረት መታደስ። ከአጠቃላዩ ትንሣኤ በመጀመር፣ሁነቶቹን እንመለከታቸዋለን።

## አጠቃላይ ትንሣኤ

በክርስቶስ መመለስ ጊዜ ሙታን ሁሉ ይነሣሉ። ኃጢአተኞቹም ሆኑ ጻድቃን ለዘላለም የሚኖር አዲስ አካል ይሰጣቸዋል።

ዮሐንስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 28 እና 29 ውስጥ ኢየሱስ በተናገራቸውና ቀጥሎ ባሉት ቃላት ይህ በትክክል ትምህርት ተሰጥቶበታል፣

> *"መቃብር ውስጥ ያሉ ሁሉ ድምጹን የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል፣መልካም የሠሩ ለህይወት ትንሣኤ፣ ክፉ የሠሩ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ"(ዮሐንስ 5፡28-29)*

ትንሣኤው አካላቸው ለጠፋ ሙታን እንኳን እንደሚሆን በተነገረን ራዕይ ምዕራፍ 20 ቁጥር 13ትን በመሳሰሉ ሥፍራዎች ተመሳሳይ ሀሳቦችን እናገኛለን። ማንም አይቀርም፣ ሰው ሁሉ ለፍርድ ይነሣል።

የአማኞችን ትነሣኤ ያገኙ አካላት በተመለከተ፣ከመበስበስና ከኀጢአት መገኘት ነጻ እንደሚሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። ከዚያ ወዲያ ኀጢአት በእኛ አይኖርም፣ ለዘላለም ፍጹም ጤና ይኖረናል።

ጳውሎስ ፊልጵሰዩስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 20 እና 21 ውስጥ፣እንዲህ ብሏል፣

> “እኛ ግን አገራችን በሰማይ ነው፣ከዚያ የሚመጣውንም አዳኝ ጌታ፣ ኢየሱስ ክርስቶስን በናፍቆት እንጠብቃለን፣እርሱም ሁሉን ለራሱ ባስገዛበት ሃይል ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል“(ፊልጵ.3፡20-21)።

በመጨረሻ ሁኔታችን፣ አሁን ኢየሱስ ያለውንና ከሞት በተነሣ ጊዜ የተቀበለውን በመሰለ ሁኔታ አካሎቻችን የከበሩ ይሆናሉ።

ያላመኑ ሰዎች አካላትም ለዘላለም ይኖራሉ፣ ነገር ግን ከኀጢአት ነጻ አይሆኑም። አካሎቻቸው እግዚአብሔር ኀጢአትን ከረገመበት እርግማን ውጤት ጋር እንደተያያዙ ይቀጥላሉ። በሚፈረድባቸው ጊዜ እርግማኑ ይጨምራል። መጽሐፍ ቅዱስ ዮሐንስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 28 እና 29፣ እና ሐዋ.ምዕራፍ 24 ቁጥር 15 በመሰሉ ስፍራዎች ስለ ማያምኑ ሰዎች በአካል መነሣት ይገልጻል። በአካል የሚፈረድባቸው መሆኑን ደግሞ፣ማቴዎስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 30፣ እና ምዕራፍ 10 ቁጥር 28 ውስጥ ይገልጻል።

ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ የሚፈጸመው ሁለተኛ ዋና ሁነት፣የመጨረሻው ፍርድ ነው።

## የመጨረሻ ፍርድ

ከአጠቃላዩ ትንሣዔ በኋላ ወዲያውኑ፣ኢየሱስ በንጉሥነት ሥልጣኑና ኃይሉ ተጠቅሞ፣በመጨረሻ ፍርድ ጊዜ ጠላቶቹን ሁሉ ያጠፋል፣ታማኞች ሕዝቦቹን ደግሞ ይባርካል። ማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር በመጨረሻው ፍርድ ይካተታል፣ከዚያ የሚያመልጥ ሰው የለም። መክብብ ምዕራፍ 12 ቁጥር 14፣ማቴዎስ ምዕራፍ12 ቁጥር 36 እና 37፣ 2 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 10፣ እና ራዕይ 20 ቁጥር 12 እና 13 በመሳሰሉት ምንባቦች ውስጥ ይህ ግልጽ ተደርጓል። እነዚህ ምንባቦች እራሳቸው ማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር እንደ ሚፈረድበት ሁሉ፣የያንዳንዱ ሰው ህይወት ሁኔታም በፍርድ ጊዜ እንደ ማስረጃ እንደ ሚቆጠርበት ያመለክታሉ። እያንዳንዱ ሀሳብ፣ቃል እና ድርጊት ይመዘናል።

ሰብዓዊ ፍጡር የወደቀና ኀጢአተኛ ስለሆነ፣በራሱ ሥራ እግዚአብሔር ፊት የሚቆም ማንኛውም ሰው፣ በዚህ ፍርድ ይፈረድበታል፣ በዘላለም ኩነኔ ሲያል

ውስጥ ይቀጣል። መልካሙ የምሥራች፣በክርስቶስ በማመን አማካይነት በጸጋ ምህረት ያገኙ ነጻ ይሆኑና፣የዘላለም ውርስ ይሰጣቸዋል።

ዮሐንስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 18 ነገሩን እንዲህ ይገልጸዋል፣

*“በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና“ (ዮሐንስ 3፡16)*

ይሄው ሀሳብ፣ዮሐንስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 24፣ 1 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 11 ቁጥር 32፣ እና 2 ተሰሎንቄ ምዕራፍ 2 ቁጥር 12 በመሳሰሉት ሥፍራዎች ተደግሟል።

*እንደሚመስለኝ፣ እንደ ዳኛ በመዋጀት ሥራው የወልድ ሚና፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር በጣም ማጉላት የሚገባን የመሆኑን ዝንባሌ ሚዛናዊ የማድረጊያ መንገድ ነው። የእግዚአብሔር ባሕርይ በመሠረቱ፣ቅዱስ ነው፣ ቅድስና ደግሞ ሁለት ዋና ዋና መልኮች አሉት፣ የጻድቅነት ደረጃዎችና ምህረት የሞላው ፍቅሩ። ስለዚህ፣ ወልድ፣ ከፍቅር የተነሣ እራሱን በመስቀል ላይ ለመስጠት የመምጣቱ ገጽታ፣ መቤዠት ለምንለው ነገር ማዕከላዊ ነው። በዚያ መቤዠት ውስጥ፣ እርሱ ቅዱስና ጻድቅ፣እንዲሁም ደረጃዎቹ ፍጹም ያልተለወጡ የመሆናቸውን እውነትም መጋፈጥ ይኖርብናል። ከገነት የአትክልት ሥፍራ አንስቶ እስከዛሬ ያው ናቸው። ሁላችንም ኀጢአት ሠርተነናል። በመሆኑም፣ስለ መስቀሉና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የመቤዠት ሥራ ላለን ጽንሰ ሀሳብ፣ የዳኛው ፍርድ አንድ ዋነኛ ክፍል መሆን አለበት። ያለዚያ፣የኀጢአትን ጽንሰ ሀሳብ የምናጠፋው ይመስለኛል። ለዚያ ኀጢአት መሠረታዊ ንሥሐና አዳኝ የሚያስፈልገን መሆኑ አይገባንም። ድርጊቱ አንድ አፍቃሪ ጣኦት መጥቶ ከችግሬ ውስጥ እንደሚያወጣኝ ይሆናል። ያ የጌታ ኢየሱስ ፍርድና ጽድቅ በመስቀል ላይ ለፈጸመው ሥራ፣ አንድ ሰው ድነትን ካገኘ በሁዋላ እንኩዋን በአማኙ ህይወት ውስጥ የሚያከናውነው ቀጣይ ሥራው፣ ሙሉ ጽንሰ ሀሳብ፣ መሠረታዊ ነው። በሰብዓዊ ፍጡር ታሪክ መጨረሻም ኢየሱስን እንደ ዳኛ ልናገኘው ነው። ስለዚህ፣ ዳኝነቱ ከምህረቱ ሁሉ ጋር እኛን የሚወክሉ እንዲሆኑ፣ህይወቶቻችን ሁሉ በዚህ የፍቅር ቅድስና እና ቅዱስ ጽድቅ ስር ይሆናሉ።(ዶር.ቢል ኡሪ)*

በመጨረሻም፣ ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ የሚከናወነው ሦስተኛ ዋና ሁነት፣የፍጥረት መታደስ ነው።

## የፍጥረት መታደስ

ኢየሱስ በሰብዓዊ ፍጡራን ላይ እንደሚፈርድና ያላመኑ ሰዎችን እንደሚያስወግድ ሁሉ፣ፍጥረትን እራሱን አስወግዶ ያድሰዋል።

2 ጴጥሮስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 10-13 የፍጥረትን መታደስ ቀጥሎ ባለው ሁኔታ ይገልጸዋል፣

*"የጌታ ቀን ግን እንደሌባ ይመጣል፣ በዚያች ቀን ሰማያት በታላቅ ድምጽ ያልፋሉ፣ የሰማይም ፍጥረት በእሳት ይጠፋል፣ምድርና በእርስዋም ላይ ያለ ነገር ሁሉ ይቃጠላል። እንግዲህ ሁሉም ነገር በዚህ ሁኔታ የሚጠፋ ከሆነ፣እናንተ እንዴት ዓይነት ሰዎች ልትሆኑ ይገባችኋል? አዎ፣ በቅድስናና በእውነተኛ መንፈሳዊነት ልትኖሩ ይገባችኋል፣ደግሞም የእግዚአብሔርን ቀን እየተጠባበቃችሁ መምጫውን ልታፋጥኑ ይገባል። በዚያን ቀን ሰማያት በእሳት ተቃጥለው ይጠፋሉ፣ የሰማያት ፍጥረት በታላቅ ትኩሳት ይቀልጣል። እኛ ግን ጽድቅ የሚኖርበትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር በተስፋ ቃሉ መሠረት እንጠባበቃለን"(2 ጴጥሮስ 3፡10-13)*

*የሰብዓዊ ፍጡራን መዋጀት፣በሌላው ፍጥረት ላይ አንድ ተጽእኖ ይኖረዋል፣ ምክንያተቱም፣ሮሜ 8፡22 እንደሚለው፣"እስከ አሁን ድረስ ፍጥረት ሀሉ በምጥ ጊዜ እንዳለው ሥቃይ በመቃተት ላይ እንደሚገኝ እናውቃለን። እርሱ ብቻ ሳይሆን፣የመጀመሪያውን የመንፈስ ፍሬ ያገኘን እኛ ራሳችን የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነታችንን በናፍቆት እየተጠባበቅን በውስጣችን እንቃትታለን" በአዳም ኀጢአት ምክንያት ፍጥረት ለጭንቀት ተጋልጦ ነበር። ይህ ጭንቀት ራሱን የሚገልጠው፣በምስቅልቅልነት፣ በብጥብጥና ሞት ነው። ይህን ፍጥረት አሁን ያለበትን ነገር፣ ጳውሎስ ህጻን እንደምትወልድ ሴት ምጥ ነው ይለዋል፣ይህ የሚያመለክተው፣ገና የሚመጣ ነገር መኖሩንና፣ከዚያም አንድ ነገር የሚወለድ፣ ፍጥረት በሙሉም ነጻ የሚሆን፣ እንዲሁም እንደገና የሚታደስ መሆኑን ነው። የመጀመሪያውን የመንፈስ ፍሬ ያገኘን እኛ ራሳችን የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነታችንን እየጠበቅን ባለንበት*

*ጊዜ አሁን፣ ፍጥረት የእውነታውን መፈጸም ይጠብቃል። አማኝ በሚከብርበት ሁኔታ እንደ ታደሰና፣ከሞት፣ከኀጢአትና መበስበስ ነጻ እንደሆነ፣ፍጥረትም በተመሳሳይ ሁኔታ ከእስራቱ ነጻ ይሆናል። ይህ የሚሆነው፣አሁን በዙሪያችን የምናየው ሞት፣መበስበስ፣መፈራረስ ወይም ምስቅልቅልነት የሌለበት አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር በሚመጣበት ጊዜ ነው።(ሬቭ.ጀምስ ማፕልስ)*

በራዕይ ምዕራፍ 22 ቁጥር 3 መሰረት፣የሰማይና ምድር መታደስ፣የኀጢአትን መገኘትና እርግማን ሙሉ በሙሉ ያስወግዳል። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ያለ ኀጢአት፣ስቃይ፣በሽታ ወይም ሞት እንዲኖሩ፣ የሰው ዘር ውድቀት ውጤቶች ሁሉ ይወገዳሉ። እንደውም ራዕይ ምዕራፍ 21 ቁጥር 4 እግዚአብሔር እንባን ሁሉ ከዐይኖቻችን የሚጠርግ መሆኑን ይነግረናል። ፍጥረት ሁሉ በእግዚአብሔር የመጀመሪያ እቅድ መሰረት ይታደሳል፣ ሕዝቦቹም በዘላለማዊው መንግሥቱ ውስጥ የማያልቅ የህይወት በረከት ይቀበላሉ። ራዕይ ምዕራፍ 21 እና 22 ውስጥ የተጠቀሰችው አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ደግሞ የመንግሥቱ መናገሻ ትሆናለች።

ራእይ ምዕራፍ 22 ቁጥር 2 የኢየሩሳሌምን አንድ ክፍል እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፣

*በወንዙ ግራና ቀኝ ...የሕይወት ዛፍ ነበረ፣ የዛፉም ቅጠሎች ሕዘቦች የሚፈወሱባቸው ነበሩ(ራእይ 22፡2)*

*የእግዚአብሔር አምሳያ ሆኖ በተፈጠረው፣ ተፈጥሮን እንዲገዛ በተደረገው ሰውና በእግዚአብሔር መካከል በፍጥረት ጊዜ የተመሠረተ ግንኙነት አለ። ስለዚህ፣ አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ሥልጣን በታች ፍጥረትን እዲገዙ ተደርገዋል፣በእነሱና በሚመሩት መንግሥት መካከል መያያዝ አለ። አዳምና ሔዋን በኀጢአት በወደቁ ጊዜ፣ድርጊቱ ያስከተለው ወጤት በአዳም ላይ ብቻ ሳይሆን፣በተፈጥሮም ላይ ነው የደረሰው። በተመሳሳይ ሁኔታ፣በሰው የመጨረሻ መዋጀት ጊዜ፣ ፍጥረት ወደ መበስበስ እሥራት እንደገባ፣ሮሜ 8 እንደሚለው፣ በመጀመሪያ በአዳምና ሔዋን እንደሆነው ማለት ነው፣ሰዎች ወደ መጨረሳ መዋጀታቸው ሲገቡ ከኀጢአት ውጤቶች ነጻ ይሆናሉ። ስለዚህ፣የእግዚአብሔር አምሳያና ከእርሱ በታች ገዥ በሆኑት፣ እንዲሁም እነሱ በሚገዙት ግዛት መካከል ግንኙነት አለ። ያ ውጤት፣ኀጢአትን፣ የሰውን ኀጢአታዊ ልምምድ በተመለከተ ማለት ነው፣እና ወደዚሁ ተመሳሳይ ልምምድ የገባውን የተፈጥሮ ውድቀት ጨምሮ የተሳሰረ ነው። በመጨረሻም፣ፍጥረት*

*ከእስራቱ ነጻ በሚሆንበት መንገድ የሰዎች ከኀጢአታቸው ነጻ መሆንም እንዲሁ ይሆናል።(ዶር.ሮበርት ሊሰትር)*

የኢየሱስን አመጣጥና ሁነቶች ካየን እንግዲህ፣የመመለሱን ውጤቶች እናጥና።

**ውጤቶች**

በዚህ ትምህርት መጀመሪያ ላይ፣ እግዚአብሔር ጽንፈ ዓለሙን የፈጠረው፣ በመንግሥቱ በክርስቶስ በኩል ክብሩን ሊገልጥና ሊያበዛ ነው በማለት ለፍጥረት ያለውን ዓላማ አጠቃለናል። የኢየሱስ መመለስ ውጤቶችም የዚህ ዓላማ የመጨረሻ ክንውን ይሆናሉ። ኢየሱስ የሚመለሰው፣እግዚአብሔር በሚወዳቸውና በሚወዱት፣በአጸፋውም በሚያገለግሉት፣ እንዲሁም በሚያመልኩት ታማኝ ሕዝቦች የሞላችውን፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በሙሉነትዋ ወደ ምድር ለማምጣት ነው።

*ሰውን በመታደግ የእግዚአብሔር የመጨረሻ ግብ፣አንድን ሕዝብ መልሶ መመሥረት ነው። ይህ መልሶ ምሥረታ፣አዳምና ሔዋን በኤደን የአትክልት ሥፍራ ከእግዚአብሔር ጋር ከነበራቸው ህብረት እንኳን የላቀ ምሉዕ ይሆናል። ከሰው ውድቀት በሁዋላ፣እግዚአብሔር የመጀመሪያውን የወንጌል ተስፋ ሰጥቷቸው፣ ከሴቲቱ ዘር ወጥቶ የእባቡን እራስ ስለ ሚቀጠቅጠው ታዳጊ ተናግሯል። የቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፣የመልሶ መመሥረቱ ሂደት መታየት ነው። ሕዘበ እስራኤል፣ የመልሶ መመሥረቱ አንድ ክፍልና የዚሁ መመሥረት ምስል ነው። ቤተክርስቲያንን ደግሞ፣ ዓለም አቀፍ ስለሆነች፣ከመልሶ ምስረታው እንኳን የላቀች ምስል ናት። ከዚያም በመጨረሻ፣ በክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ጊዜ፣እግዚአብሔር ከሰው፣ በእምነት በኩል ክርስቶስን ወደ ማወቅ ከመጡት ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሚያደርግበት ጊዜ ይሆናል። እነርሱም፣ሰይጣን ከዚያ በሁዋላ ሊያጠቃ በማይችልበት፣ኀጢአት በማይኖርበት ፍጹም ሁኔታ ውስጥ ይደሰታሉ፣ ለዘላለምም እግዚአብሔርን በፍጹም ሁኔታ ያከብሩታል።(ዶር.ጀፍ ሎውማን)*

የኢየሱስ ሰማያትንና ምድርን ፍጹም ማድረግ ውጤቶች፣በብዙ መንገዶች ሊጠቃለሉ ይችላሉ፣በዚህ ትምህርት ውስጥ ግን በሁለት እንከፍላቸዋለን። መጀመሪያ፣የፍጻሜው ውጤት የሆነውን የእግዚአብሔር ክብር ጉዳይ እንመለከታለን። ሁለተኛ ሰብዓዊ ፍጡራን በሚኖራቸው የመዋጀት ደስታ ላይ እናተኩራለን። በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን ክብር ጉዳይ እንመልከት።

**የእግዚአብሔር ክብር**

*ሥሉስ የሆነው እግዚአብሔር ለመዋጀታችን በመሥራቱ ለዘላለም ክብርን ይቀበላል ብየ አስባለሁ። እግዚአብሔር ይህን ያደረገው፣ለክብሩ፣ጽድቁን ብቻ ሳይሆን፣ጻድቅነቱን ለመገለጥና፣ የማይለወጥ መሆኑን፣የህጉን ፍጹም ቅዱስነት ብቻ ሳይሆን፣ ጥበበኛ መሆኑንም ለማሳየት ነው። ስለሱ የተነገሩት ባህርያት ሁሉ አሉት፣ ቢሆንም ኀጢአተኞችን ይምራል፣ይቅር ይላል ያጸድቃል። ነቢዩ፣"እንዳንተ የሚምር አምላክ ማነው፣እንዳንተስ ጸጋ ያለው ማነው?" በማለት ጠይቋል። ስለዚህ ይህ ለእግዚአብሔር ክብር ነው። ለኀጢአተኞች ድነት ነው፣የዚህና የታሰበው ውጤቱ የመጨረሻ ግብ፣ የእግዚአብሔር ክብር በዘላለም ሁሉና ሁልጊዜ እያደገ በሚሄድ መጠን እንዲገለጥ ነው።(ዶር. ቶማስ ኔትልስ)*

ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ፣በመንግሥቱ ላይ እንደ ንጉሥ የሚኖረው አገዛዝ ወደ ከፍተኛና አጅግ ወደ ተከበረ ሁኔታ ከፍ ይላል። እናም፣ ለእግዚአብሔር ክብርን የመስጠቱ ግብ፣ ሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ የኢየሱስን ገዥነት በሚቀበልበትና ለሥልጣኑ በሚሰግድበት ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል።

ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 9-11 ባለው ክፍል እንደጻፈው ይሆናል፣

*"ስለዚህ እግዚአብሔር እጅግ ከፍ አደረገው፣ከስምም በላይ የሆነውን ስም ሰጠው፣ ይሄውም በሰማይና በምድር፣ ከምድርም በታች ጉልበት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይንበረከክ ዘንድ፣ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው" (ፊልጵስዩስ 2፡9-11)*

የእግዚአብሔር ቸርነት፣ ክብርን ያመጣለታል፣ምክንያቱም፣በፍቅርና ቸርነቱ፣ንስሐ ለሚገቡ ኀጢአተኞች ይቅርታ ያደርጋል፣ከምናስበው በላይ በሆነ መንገድም ይባርከናል። እኛም በአጸፋው፣እናመሰግነዋለን፣ መልካምነቱንም እናውጃለን።

ጳውሎስ ኤፌሶን ምዕራፍ 2 ከቁጥር 6-7 ባለው ክፍል እን

*እግዚአብሔርም ከክርስቶስ ጋር አስነሣን፣ በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን፣ይሄውም በሚመጣው ዘመን፣*

*በክርስቶስ ኢየሱስ በቸርነቱ የገለጠልንን ወደር የሌለውን የጸጋውን ባለ ጠግነት ያሳይ ዘንድ ነው።(ኤፌሶን 2፡6-7)*

ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ፣ ለታማኝነታችን እንሸለማለን፣ታማኞች የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሁሉ ደግሞ፣አዲስ ሰማይና ምድርን ይወርሳሉ። ይህ ራዕይ ምዕራፍ 21 ከቁጥር 1-5 ውስጥ፣እግዚአብሔር ከአዳምና ሔዋን ጋር ኤደን አትክልት ሥፍራ ውስጥ ከነበረው መገኘት በላቀ ሁኔታ ከእርሱ ጋር እንደምንሆን ያስተምራል።

*በግልጽ እንደሚታወቀው፣ከውድቀት በፊት ሰዎች ነጻ የሆነና ያልተመሰቃቀለ ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር ነበራቸው።ነገር ግን ከውድቀት በኋላ፣እግዚአብሔር፣ ከእርሱ ጋር የወደፊት ግንኙነትን የሚጠብቅ መዋጀትን ማኖሩን የሚያመለክት ሁኔታ አለ። ይህ ደግሞ ከውድቀት በፊት ከነበረው ይልቅ ሙሉና የበለጠ ነው። አዳም የእግዚአብሔር ወዳጅ ተባለ፣የማንኛውም አማኝ ጥቅም ግን ልጅ መባሉ ነው፣ በዚህ ቃል ውስጥ ከተጠቆመው ነገር ጋር በተዛመደ ሁኔታ ከፍ ያለ መቀራረብ የመኖሩን እውነት ብዙ ሰዎች አመልክተዋል፣ይህ የሚያስረዳው፣እንደገና ወደ አትክልቱ ሥፍራ የማንመለስ መሆኑን ነው። የምንጉዋዘው፣ ወደ አዲስቱ ኢየሩሳሌም ነው፣ያ ትልቅ ሥፍራ፣አዲሲቷ ኢየሩሳሌም፣አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር፣በፊት ወደ ነበርንበት የማንመለስበት፣መሆንና አለመሆኑን ለመረዳት በመጽሐፍ ቅዱሳዊው አስተምህሮ ጉዞ ውስጥ ሁሉ እድገት የሚኖር ይመስላል።(ዶር. ሳይመን ቫይበርት)*

*ውድቀት፣የሆነ ነገር ወይም ያለፈ በመሆኑ ደስተኞች ነን ወይ? የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ፣በመጀመሪያ፣ የሰው ውድቀት፣እግዚአብሔርን እምቢ የማለት፣ አሰቃቂ ነገር መሆኑን ማወቅ የሚጠቅም ይመስለኛል። አሳዛኝ ነገርና በታላቁ የሰማይ ንጉሥ ላይ የሚፈጸም ክህደት ነው። እናም አሰቃቂውን የሲኦል ስቃይ በፍጹም አሳንሰን ልንመለከት አይገባም። ነገር ግን የእግዚአብሔር ልዑል እቅድ ሲከናወን በምናይበት ጊዜ፣በፍጻሜው ወቅት፣አዳምና ሄዋን በንጽህናቸው አንደነበሩበት ጊዜ በአትክልቱ ሥፍራ ብንሆን ኑሮ ከሚሆንልን በጣም የተሻለ ውጤት እንደሚሆንልን እንረዳለን። በመታደግ ውሰጥ የሚኖረን ነገር፣ንጹህ የመሆን ነገር ብቻ ሳይሆን፣እንደገና ከሥላሴ ጋር ወደ ህብረት የምንገባበት ነው። በክርሰቶስ መዋጀታችንና በእርሱ ካለን እምነት የተነሣ፣ወደ ሥላሴ፣ማለት አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሕብረት ለዘላለም ተጠርተናል፣እናም፣የመለኮታዊ በህርይ ተካፋዮች እንሆናለን፣ከክርስቶስ ጋር ወራሾች። በክርስቶስ ያለንበትን ሁኔታ*

*በምንመዝንበት ጊዜ፣ በጣም በእርግጠኛነት፣እንደ አዳምና ሄዋን በአትክልቱ ሥፍራ ብንኖር፣ከሚሆንልን ነገር በጣም የላቀ ነው። ስለዚህ፣ከውድቀት የተነሣ የሚመጣ አስደናቂና ሉዓላዊ በረከት አለ። የሚያሳዝን ሳይሆን ቀርቶ አይደለም፣የሚሆነው ነገር የሚሆነው፣በእርግጠኛነት የእግዚአብሔር መልካምነትና ሀይል በሌላ መንገድ ሊኖረን ከሚቻለን እጅግ የላቀ ነገር ስለሚሠራ ነው።(ዶር.ኬ. ኤሪክ ቶኤንስ)*

እርግጥ፣እግዚአብሔርን የሚያከብርና ለሰብዓዊ ፍጡራን ሁሉ እንደ ማስጠንቀቂያ ማገልገል የሚገባው የኢየሱስ መመለስ ሌላ ጎንም አለ። ጌታ ሕዝቦቹን ከመባረክ በተጨማሪ፣ እንደ ተዋጅ እና ንጉሥ ሊቀበሉት ያልፈለጉትን ይረግማል። የእነሱ መቀጣት፣የቅድስናውን ክብር ስለ ሚጠብቅ ያከብረዋል፣ጻድቅነቱን ይገልጻል፣ሕዝቦቹንም ከኀጢአት ተጽእኖና ስቃይ ነጻ ያደርጋቸዋል። እንደ ራዕይ ምዕራፍ 19 ቁትር 1 እና 2 ባሉ ምንባቦች መሠረትም፣ ጻድቃን የእግዚአብሔር ሕዝቦችም በኀጢአተኞች ላይ በሚሰጠው ፍርድ ደስተኞች ይሆናሉ። ነገር ግን፣ እስከዚያ ድረስ ክርስቲያኖች በዚህ ሀሳብ ደስተኞች አይሆኑም። ከዚያ ይልቅ፣እራሳቸውን በክርስቶስ የሚገኘውን ድነትና የይቅርታ ወንጌል ለማወጅ ሥራ ይሰጣሉ፣በተቻለ መጠን ብዙ ሰዎች ከዚህ አስከፊ እጣ እንዲያመልጡ ለማድረግ።

በፍጻሜው ጊዜ ስለ ሚገለጸው የእግዚአብሔር ክብር ከተመለከትን እንግዲህ፣ ወደፊት አማኞች ስለሚኖሩበት የድነት ደስታ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን እንመልከት።

## የድነት ደስታ

መጽሐፍ ቅዱስ፣አማኞች በድነታቸው ጊዜ የሚያገኙዋቸውን ቢያንስ ሦስት የማያቋርጥ ደስታ ምንጮች ይጠቅሳል። ከነዚህ ሁሉ የሚልቀው፣ምናልባት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሙሉ ሕብረት የሚኖረን መሆኑ ነው።

አዳምና ሄዋን በኤደን የአትክልት ሥፍራ ኀጢአት ከሠሩ በኋላ፣ከእርስ በርሳቸውና ከእግዚአብሔር ተደበቁ። እግዚአብሔር ረገማቸው፣ልዩ ከሆነው የህልውናው ሥፍራም ተባረሩ። በመጨረሻ ጊዜ ግን፣ኢየሱስ ሰብዓዊ ፍጡርን ወደ ነበረበት ሥፍራ ይመልሳል። በመሆኑም፣ ክብሩን በዐይናችን እናይ ዘንድ፣ አካላዊ በሆነ መንገድ ወደ እግዚአብሔር ልዩ መገኛ በልዩ ሁኔታ መግባት ይፈቀድልናል። ይህ እውነት፣እንደ ዮሐንስ መዕራፍ 17 ቁጥር 24 እና ራዕይ 21 ቁጥር 3 ባሉት ሥፍራዎች በግልጽ ትምህርት ተሰጥቶበታል። የአራተኛው ክፍለ ዘመን ጳጳስ የነበረው የሂፖው አውግስቲን፣ የእግዚአብሔር

ከተማ በሚለው ቁጥር 22 መጽሐፉ፣ምዕራፍ 30 ውስጥ፣ ይህን በረከት በአጭሩ የገለጸበትን ሁኔታ ተመልከቱ፣

*የመልካም ነገር ባለቤት እግዚአብሔር ራሱ፣ተስፋ የሰጠበትና የበለጠ ወይም የተሻለ ነገር የሌለበት ስጦታ አለው:: በነብዩ በኩል እንዲህ በመባል የተነገረው ቃል ትርጉም ታዲያ ምንድነው፣"አምላካችሁ እሆናለሁ፣እናንተም ሕዝቤ ትሆናላችሁ"፣ "እርካታቸው እሆናለሁ፣ሰዎች በክብር የሚመኙት--ህይወት፣እና ብልጽግና፣ ምግብ፣ የተትረፈረፈ፣ ክብር፣ ሰላም፣ መልካም ነገሮች ሁሉ" ይህ የሐዋርያው አባባል ትክክለኛ ትርጉም ነው፣"እግዚአብሔር ሀሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ" ፍጻሜ የሌለውና በመጨረሻ የሚታየው ምኞታችን ይሆናል፣ያለማቋረጥ የሚወደድ፣ያለመሰልቸት የሚወደስ:: ይህ የሚቀጥል ፍቅር፣ይህ ተግባር፣እንደዘላለማዊ ህይወት፣በእርግጥ ለሁሉም ይሆናል::*

አማኞች የሚያጣጥሙት የመዋጀት ደስታ እርስ በርስ የሚደረግ ፍጹም ሕብረት ነው:: የአዳም ኀጢአት፣ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ከማጥፋት በተጨማሪ፣ ሰብዓዊ ግንኙነቶችንም አበላሽቷል:: ራዕይ ምዕራፍ 22 ቁጥር 2 እንደሚለው ግን፣ሙሉ በሙሉ በምንዋጅበት ጊዜ፣ሕዝቦች ይፈወሳሉ:: ጦርነቶች ይቆማሉ፣ግፍ ያበቃል፣እናም ግንኙነቶች ሙሉ በሙሉ ይታደሳሉ:: ዓለም ሞላዋ፣ሰላማዊ፣ወዳጅነት ያለባት፣አንዱ ሌላውን የሚወድበት እንዲሁም፣ የሚያገለግልበትና ቤተሰባዊ ይሆናል::

በመጨረሻም፣በሦስተኛነት የምንጠቅሰው የመታደግ ደስታ፣በአዲቱ ሰማይና ምድር ከኢየሱስ ጋር የምንነግሥ መሆናችን ነው::

ጳውሎስ፣2 ጢሞቲዎስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 12 ውስጥ ቀጥሎ ያለውን በጻፈ ጊዜ ይህን ገልፆል፣

*ብንጸና ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን (2 ጢሞ.2፡12)*

ከክርስቶስ ጋር የመንገሣችን ነገር ራዕይ ምዕራፍ 2 ቁጥር 26 አና 27፣ምዕራፍ 3 ቁጥር 21፣ እና ምዕራፍ 22 ቁጥር 5 ውስጥም ትምህርት ተሰጥቶበታል::

አዳምና ሄዋን፣ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረው፣በእግዚአብሔር ጌትነት ሥር በፍጥረት ላይ እንዲነግሡ በኤደን አትክልት ሥፍራ ተደርገው ነበር:: በአዳም ኀጢአት ምክንያት የመጣው እርግማንና ብልሹነት ግን፣ሰው

የእግዚአብሔርን የመጨረሻ ዓላማ በሚፈጽም መንገድ ይህን እንዳያደርግ ከለከለው። ኢየሱስ ግን፣በመስዋእትነቱና በታዛዥነቱ፣አዳም ሊሠራ ያልቻለውን ማድረግ ጀመረ። አሁን እንደ ቃል ኪዳናችን እራስነት በመቆም፣ በመላው ፍጥረት ላይ ነግሷል። በዓለም ፍጻሜ ደግሞ፣ የተዋጀው ሰብዓዊ ፍጡር፣ እግዚአብሔርን በሚያከብርና ፍጥረትን ሁሉ በሚጠቅም መንገድ ፍጥረትን ይገዛል።

ክርስቲያኖች፣ በተስፋ መንፈስ፣ መዋጀት ለሞላበት የወደፊት ተስፋችን አጸፋ ልንሰጥ እንችላለን። ተስፋ፣አወንታዊ የሆነው የወደፊት ነገር አርግጠኛ እምነት ነው። አስደናቂው የተስፋ ባህርይ፣ ተስፋ የማንቆርጥ፣ ታጋሾች፣ጽኑዎች፣ በአሁኑ ጊዜም፣የአመንንበት ነገር ይፈጸማል በሚል እምነት የጸና ደስታ እንዲኖረን ማድረጉ ነው።

በተወሰነ እይታችን ምክንያት፣ ያለመጽናት ወይም እርግጠኛ ያለመሆን ተፈጥሯዊ ድካም በሚኖርብን ጊዜ፣ ዛሬ የምንሠራው ሥራ፣ ዋስትና ባለው የእርግጠኝነት ስሜት ወደ ፊት ያራምደናል።

### ማጠቃለያ

ስለቤዛችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀረበው በዚህ ትምህርት የኢየሱስን፣ የእግዚአብሔርን ልጅ፣ ማንነትና በአራቱ የተለያዩ ጊዜያት፣ማለት በዘላለም፣ ከጽንፈ ዓለማት መፈጠር በፊት፣ በፍጥረት መጀመሪያ ጊዜ፣ በረጅሙ የፍጥረት ጊዜና፣በወደፊቱ የፍጻሜ ጊዜ ሥራውን ተመልክተናል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ያለጥርጥ ፍጹም ተወዳጅ፣ ከዚህ ቀደም ያልታየ፣ ረቂቅና ታላቅ ሰው ነው። ዛሬም ይኖራል፣ በሰማይ ካለው ዙፋኑም በፍጥረት ሁሉ ላይ ንጉሥ ነው። በሙሉ ረቂቅነቱ ልናውቀውና ልንረዳው አንችላለን ብለን ተስፋ አናደርግም። ነገር ግን፣ በዚህ ትምህርት አጠቃላይ እይታ፣እርሱን በሚያከብርና ለሕዝቡ በሚጠቅም ሁኔታ ስለ ኢየሱስ እንድናስብ ያዘጋጀናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን